# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

## ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

## DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

## OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

2ኛ ዓመት ቁጥር 4
አርባ ምንጭ ታህሳስ 5 ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 4 Arba Minch;
December 15, 2023


## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፮**


**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የፍርድ ቤቶች አዋጅ-----ገፅ**


## አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፮

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የፍርድ ቤቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል መንግስቱና በክልሎች የተከፋፈለ በመሆኑ፣

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክም ሆነ

## CONTENT

**Proclamation No. 6/2023**


**South Ethiopia Regional State Courts Proclamation-----Page**


## PROCLAMATION NO. 6/2023

## THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE COURTS PROCLAMATION

WHEREAS, in the Federal Democratic Republic of Ethiopia, judicial power is devided both in Federal and Regional Level;

WHEREAS, it is stipulated in the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the state that any person has the right to submit a justiciable matter to a court of law to

በክልሉ ሕገ-መንግስት የተደነገገ በመሆኑ፤

የክልሉ ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን ነፃነትና ተጠያቂነት ባለው አኳኋን ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ተገማች የሆነ አገልግሎት በመስጠት ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚጠበቅባቸውን ሚና የሚወጡበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የዳኝነት ሥርዓቱን ለማጠናከር የክልል ፍርድ ቤቶች በበጀት ምደባና አስተዳደር፤ በሰው ሀብት ቅጥርና ምደባና እንዲሁም አስተዳደር ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን የሕግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው

obtain a decision or judgment;

WHEREAS, it is necessary to establish a system in which the courts of the region perform their duties in an independent and accountable manner by providing effective, efficient, accessible and reliable services for the rule of law, respect for human and democratic rights;

WHEREAS, it is necessary to establish a legal framework and operating system to strengthen the judicial system in which regional courts can work independently, manage their own budget, recruit and assign their non-judicial personnel, allocation of human resources, as well as their management;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 54 Sub-Article 3(a) of the Constitution of the South Ethiopia Regional State, it is hereby proclaimed as follows:-

## Part One
## Generals

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "the South Ethiopia Regional State Courts Proclamation No.6/2023"

### 2. Definition

In this proclamation, unless the context

ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) “ሕገ-መንግሥት” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግሥት ነው፤
2) “ክልል” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤
3) “የክልል ምክር ቤት” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ክልል ምክር ቤት ነው፤
4) “ፍርድ ቤቶች” ማለት በክልሉ ህገ መንግሥት መሠረት የተቋቋሙት ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ናቸው፤
5) “ዋና ጉባኤ” ማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የተቋቋመ የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባኤ ነው፡፡
6) “ንዑስ ጉባኤ” ማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤትና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ የተቋቋመ የዳኞች አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ ነው፡
7) “የፍርድ ቤት ጉባኤ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 ላይ የተመለከቱትን ተግባራት የሚፈፅም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ ነው፤
8) “የመንግስት ባለሥልጣን” ማለት የክልል ምክር ቤትና የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት፣ ከቢሮ ሃላፊ ደረጃ በላይ የሆኑ የክልል መንግስት ሃላፊዎች፣ የቢሮ

requires otherwise:-

1) "**Constitution**" means the Constitution of South Ethiopia Region;
2) "**Region**" means the South Ethiopia Region;
3) **"State Council"** means the South Ethiopia Regional State Council;
4) **"Courts"** means the Supreme Court, High Court, Woreda or City Administration Court of First Instance established under the Constitution of the State;
5) **"Council"** means Judicial administration council established at Supreme Court level ;
6) **“Sub-council”** means Judicial administration sub-council established at Supreme and High Court level ;
7) **“Court plenum”** means the Regional Courts plenum that executes the activities stipulated under article 53 of this proclamation;
8) **"Government Official"** means members of the State Council and the Council of Nationalities, Officials above rank of Heads of Bureau, Heads

ኃላፊዎች፣ ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የክልል ባለሥልጣናት፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና የከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንቶች ናቸው፡፡

9) “ዳኛ” ማለት በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባኤ አቅራቢነት የዳኝነት ተግባራትን እንዲያከናውን በክልሉ ምክር ቤት የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

10) “ረዳት ዳኛ” ማለት በዳኝነት ስራ ዳኛን በማገዝ እንዲሰራ የተመደበ የህግ ባለሙያ ነው፡፡

11) “የጉባዔ ተሿሚ” ማለት እንደአግባብነቱ በዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ ወይም በንዑስ ጉባኤ የሚሾም የፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የፕሬዚደንት አማካሪ፣ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ፣ የዋና ጉባዔው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፤ የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ አቤቱታ መስማትና መወሰን ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት፣ የምድብ ችሎት አስተባባሪ፣ ሬጅስትራር፣ ተከላካይ ጠበቃ፣ ወይም ቃዲ ሲሆን በዋና ጉባኤም ሆነ በንዑሳን ጉባኤዎች የሚሾሙ ሌሎች ሰዎችን ያጠቃልላል፤

12) "የአስተዳደር ሠራተኛ" ማለት ከዳኛና

of Bureau, Deputy Heads of Bureau and Officials of equivalent rank, Judges of the Regional Supreme Court and Presidents of the High Courts;

9) "**Judge**" means a natural person appointed by the State council, on the recommendation of the State Judicial Administration council, to perform judicial functions;

10) "**Assistant Judge**" means legal professional assigned to work by assisting judges;

11) "**Council Appointee**" means the Head of the Office of the President, the President Advisor, the Head of the Administrative and Finance Department, the Head of the Office of the Judicial Administration Council, the Head of the Office of the Defense Lawyers, the Head of the Office of the Judicial Administration Sub-Council, Hearing and Judgment Core Process Owner, Bench Court Coordinator, the Registrar, the Defense lawyer, or the Qadi, appointed by the judicial administration council or the Sub-Council as appropriate; and includes other people appointed by the respective judicial council;

12) "**Administrative Staff**" means any

ከዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚ ውጭ ያለ ማንኛውም የፍርድ ቤት ሠራተኛ ነው፤

13) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

14) በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ አነጋገር የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የክልል ፍርድ ቤቶች መቋቋም፣ አደረጃጀትና አስተዳደር

### ንኡስ ክፍል አንድ
### ክልል ፍርድ ቤቶች መቋቋምና አደረጃጀት

3. የክልል ፍርድ ቤቶች መቋቋም

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ሙሉ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ተቋቁመዋል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የክልል ምክር ቤት የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የክልሉን አስተዳደራዊ መዋቅር መከተል ሳያስፈልገው ተጨማሪ የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

personnel of the court other than a judge and an appointee of the Judicial Administration Council;

13) **"Person"** means any natural or juridical person;

14) Any expression in this proclamation in the masculine gender includes the feminine.

## Part Two
## Establishment, Organization and Administration of the Regional Courts

### Sub-Section One
### Establishment and Organization of the Regional Courts

**3. Establishment of the Regional Courts**

1) The Regional Supreme Court, High Courts and Woreda or City Administration Courts are hereby fully recognized and established by this Proclamation;

2) Notwithstanding to the provision of sub-article (1) of this article, when it deems it necessary to ensure access to the judiciary service, State Council may establish additional woreda or City Administration First Instance Courts and High Courts without having to follow the administrative structure of the Region.

## 4. የክልል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት

1) የክልል ዳኝነት አካል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤትንና ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን የያዘ ነው፤

2) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት በዞን ዋና ከተሞች፣ ለከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በወረዳ ዋና ከተሞች እና ለወረዳ ፍርድ ቤቶች ለተወሰኑ ቀበሌዎች ማዕከል በሆኑ ስፍራዎች ምድብ ችሎቶችን በቋሚነት ሊያደራጅ ይችላል፡፡

3) ምድብ ችሎት የሚቋቋሙበት ሁኔታ፤ አደረጃጀት እና አሠራር የክልሉ ዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባኤ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 5. የጠቅላይ ፍርድ ቤት አደረጃጀት

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት፣ ዳኞች፤ ቃዲዎች፣ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ ተሿሚዎች፣ የፕሬዚደንት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የፕሬዚደንት አማካሪ፣ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊና እንዲሁም የአስተዳደር ሠራተኞች ይኖሩታል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(1) የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሥሩ ፕሬዚደንት

## 4. Organization of the Region Courts

1) The Regional Judicial Body shall consists of the Supreme Court, the High Court and the Woreda or City Administration First Instance Court;

2) The Regional Supreme Court, as may be necessary, permanently organize Bench courts for the Supreme Court in Zonal Cities, for the High Courts in Woreda towns and for Woreda Courts in certain kebeles where it is centre for them.

3) The condition, organization, and procedure for the establishment of a Bench courts shall be determined by a regulation to be issued by the Regional Judicial administration Council.

## 5. Organization of the Supreme Court

1. The Regional Supreme Court shall have President, Vice-President, Judges, Qadis, Judicial Council appointees, Head of President Office, President Advisor, Head of Administrative and Finance department and Administrative Staffs;

2. Notwithstanding to the provisions of sub-article (1) of this article, the Regional Supreme Court shall have Office of the

ጽሕፈት ቤት፣ አቤቱታ መስማትና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ጽ/ቤት፣ ዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ይኖሩታል፤

3) የፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት፣ የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እና የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት፡-

ሀ) የየራሳቸዉ ኃላፊ እና ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሯቸዋል፡፡

ለ) የእነዚህ ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎች ተጠሪነታቸዉ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት በዋና ጉባኤ ይሾማሉ፡፡

4) የፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤትና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ እንዲሁም የፕሬዚደንት አማካሪ ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

5) የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባር በክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ይወሰናል፡፡

6) የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ እና የፕሬዝዳንቱ አማካሪ በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት በአቢይ ጉባኤ ይሾማሉ፡፡

President, Office of Judicial Administration Council, Office of Hearing and Judgement Core Process, and the Public Defenders office;

3. Office of the President, Judicial Administration Council and Office of the Public Defenders shall have:-
   a) Necessary staffs and office heads.
   b) These office heads are appointed by the Judicial Administration Council up on the recommendation by the President and are accountable to him;

4. The powers and duties of the Office of the President and its head and president advisor shall be determined by a directive to be issued by the Supreme Court;

5. The power and functions of the Judicial Administration Council Office Head shall be determined by Judicial Administration Proclamation of the Region.

6. Head of Administrative and Finance department and Presidential Adviser shall be appointed by the Judicial Administration Council up on the recommendation by the President.

## 6. የከፍተኛ ፍርድ ቤት አደረጃጀት

1) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪነቱ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት፣ ዳኞች፣ ቃዲዎች፣ የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎች እና የአስተዳደር ሠራተኞች ይኖሩታል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥሩ፤ ፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት፣ ንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እና ተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት ይኖሩታል፡፡

3) የፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት፣ የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እና የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት የየራሳቸው ኃላፊ እና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖራቸዋል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሱ ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ በፕሬዚደንቱ አቅራቢነት በንዑስ ጉባዔው ይሾማሉ፣

5) የፕሬዚደንት ጽሕፈት ቤት እና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ዝርዝር ሥልጣን እና ኃላፊነት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

6) የንዑስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት እና የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ዝርዝር ሥልጣን እና ኃላፊነት

## 6.Organization of the High Court

1) The High Court shall be accountable to the Regional Supreme Court and shall have President, Vice-President, Judges, Qadis, appointees of Judicial Administration Sub-Council and administrative staffs;

2) Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this article, High Court shall have Office of the President, Judicial administration sub-council office and office of public defenders;

3) Office of the President, office of the Judicial administration sub-council and the office of public defenders shall have their own head and necessary staff for their work;

4) The heads mentioned under sub-article 2 of this Article are accountable to the President and are appointed by the Judicial administration sub-council up on the proposal of the President;

5) Detail powers and functions of the Office of the President and Head of the Office shall be determined by the directives to be issued by the Supreme Court;

6) The detail powers and functions of the office of the judicial administration sub-council and the head of the office shall be in accordance

በክልል የዳኝነት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**7. የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አደረጃጀት**

የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪነቱ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ ፕሬዚደንት፣ ዳኞች፣ ቃዲዎች፣ የጉባኤ ተሿሚዎች እና የአስተዳደር ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**ንኡስ ክፍል ሁለት**

**የዳኝነት ነጻነትና ተጠያቂነት**

**8. የዳኝነት ነጻነት**

1) በየትኛውም እርከን የሚገኝ የክልል ፍርድ ቤት ወይም ዳኛ ከማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ወይም ሌላ አካል ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ሥራውን በሕግ መሰረት ያከናውናል፤
2) ዳኞች ስራቸውን ከማንኛውም የውስጥና የውጭ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው በማከናወን በሕግና ፍሬ-ነገር ላይ የተመሰረተ ፍርድ፣ ብይን፣ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣሉ፤
3) ማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ማንኛውም ሰው የክልሉን ፍርድ ቤቶች ተቋማዊና የዳኞችን ግለሰባዊ ነጻነት የማክበር ግዴታ አለበት፤

with the proclamation on the establishment of Region Judicial Administration.

**7.Organization of the Wereda or City First Instance Court**

Wereda or City First Instance Court shall be accountable to the High Court and shall have a president, judges, qadis, judicial administration council appointees, and administrative staffs.

**Sub-Section Two**

**Judicial Independence and Responsibility**

**8.Independence of the Judiciary**

1) A court or a judge at any level in the region shall act in accordance with the law, free from any influence and interference of any government body, official or other body;
2) Judges shall conduct judicial proceedings in a manner of independence from any internal or external influence, and base solely on law and substance while issuing judgments, ruling, decisions, or orders;
3) Any Government body, government official or any other person shall have duty to respect the institutional and individual independence of the Regional Courts;

4) ማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ማንኛውም ሰው በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የማክበርና የመፈጸም ግዴታ አለበት፤

5) የክልሉ ፍርድ ቤቶች በበጀት፣ በሰው ኃይል አስተዳደር እና በውስጥ አሰራራቸው እራሳቸውን ችለው ይሠራሉ፡፡

4) Any Government body, government Official or any other person shall be obliged to respect and carry out the decisions, judgements, ruling or orders issued by the court at any level;

5) The Regional Courts shall work independently in administration of budget, human power and their internal affairs.

## 9. የዳኝነት ተጠያቂነት

1) በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ ከተሰጠው ኃላፊነት አንጻር በሕግ መሠረት ተጠያቂነት አለበት፤
2) ዳኞች በያዙት ክርክር ሂደት ተከራካሪ ወገኖችን ያለአድሎዎ በእኩልነት የሚያስተናግዱ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርባቸዋል፤ በተለይም በወንጀል የተከሰሱ ወይም በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎችን አያያዝ ሁኔታ የመከታተል፤ ሰብአዊ መብቶቻቸውን የማክበር እና የማስከበር የእነዚህ መብቶችን ጥሰት የሚመለከት አቤቱታ በቀረበ ጊዜም ጉዳዩ አግባብ ባለው አካል ተጣርቶ ተገቢው እንዲፈፀም ትዕዛዝ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው፡፡
3) በሌሎች ሕጎች የተመለከተው እንደተጠበቀ

## 9.Judicial Accountability

1) Judge of the Regional Court at any level shall be legally responsible in respect of power entrusted on him;
2) Judges shall ensure the impartiality and equality of the services in the litigation of parties; in particular, following the treatment of people accused of crimes or in custody; respect and causes human rights to be respected, when a complaint is filed regarding the violation of these rights, they are responsible for calling the matter to the appropriate body and giving an order for the appropriate action to be taken.
3) Notwithstanding to the provisions of other laws, if any judge is found guilty of any

ሆኖ ማንኛውም ዳኛ የዲሲፕሊንና የሥነ-ምግባር ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ የዲሲፕሊን ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት

## የፍርድ ቤቶች በጀትና የሰዉ ሀብት አስተዳደር

### 10.የፍርድ ቤቶች በጀትና የበጀት አስተዳደር

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሥራው የሚያስፈልገውን ጥቅል በጀት በማዘጋጀት በቀጥታ ለክልል ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ የጸደቀለትንም በጀት ያስተዳድራል፤
2) የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥሩ ያሉ ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ ለሥራ የሚያስፈልገውን ጥቅል በጀት በማዘጋጀት በቀጥታ ለዞን ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፣ የጸደቀለትንም በጀት ያስተዳድራል፤
3) ለክልል የዳኝነት አካል የሚመደበው በጀት ፍርድ ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ኃላፊነት በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
4) የክልል ወይም የዞን ምክር ቤቶች ለዳኝነት አካል ጥቅል በጀት ሲመድቡ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ስፋትና መሰረታዊ ፍላጎት ያገናዘበ በጀት ሊመደቡ ይገባል፡፡
5) የክልል ፋይናንስ ቢሮ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ

misconduct, he shall be liable in accordance with the regulation of judicial discipline.

## Sub Section Three

## Courts Budget and Human Resource Administration

### 10. Budget and Budget Administration of Courts

1) The Regional Supreme Court shall prepare and submit the total budget necessary for its work to the State Council for approval and administer the approved budget;
2) Zonal High Court, including the courts under it, prepares the whole budget required for work and submits it directly to Zonal Council and administers the approved budget;
3) The budget allocated to the regional judiciary shall be sufficient to fully carry out their powers and functions.
4) The State or Zonal Councils while allocate a budget for the judiciary, shall take into account the work load and the basic needs of the courts.
5) The Regional Finance Bureau shall, up

ቤት በምክር ቤቱ የጸደቀውን ጥቅል በጀት የፋይናንስ አሠራርን ተከትሎ በሚያቀርበው መጠየቂያ መሠረት በየሩብ ዓመቱ መጀመሪያ ሳምንት ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የባንክ ሒሳብ ማስገባት አለበት፤

6) የዞን ፋይናንስ መምሪያ፣ የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት ለዞን፤ ለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት የጸደቀውን ጥቅል በጀት የፋይናንስ አሠራርን ተከትሎ በሚቀርበው መጠየቂያ መሠረት በየሩብ ዓመቱ መጀመሪያ ሳምንት በየፍርድ ቤቱ ባንክ ሒሳብ ማስገባት አለበት፤

7) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ ለክልል ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤

8) የዞን፤ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ ለየምክር ቤቶቻቸው ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፤

9) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና ከሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የበጀት ማካካሻ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው፡፡

on the financial request from the Supreme Court, deposit the approved budget in the first week of every quarter into the bank account of the Supreme Court;

6) Zonal Finance Department, Woreda or City administration Finance Office, up on the financial request from the respective court, shall deposit the budget in the court's bank account in the first week of every quarter;

7) The Regional Supreme Court shall be responsible to submit a budget report to the State Council;

8) Zonal High Courts, Woreda or City Administration Courts shall submit a budget report to their respective Council;

9) The Region Supreme Court shall have the right to request budget compensation from the Federal Supreme Court for the judicial services rendered by the Regional Supreme Court and High Courts.

## 11.የክልል ፍርድ ቤቶች የሰው ኃብት አስተዳደር

1) የክልሉ ፍርድ ቤቶች የየራሳቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች የመመልመል፤ የመቅጠር፤ የመመደብ እና የማስተዳደር ሙሉ ነጻነት አላቸው፤
2) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለዳኝነት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የአስተዳደር ሠራተኞችን የሥራ መደቦችን፤ ደረጃዎችን እና መመልመያ መስፈርቶችን በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች የማዘጋጀት ሙሉ ነጻነት አለው፤
3) የክልል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት፣ዝውውር፣ ስልጠና፣ ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም፣ የዲሲፕሊን ጉዳይ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የክልል ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተደነገገዉ በምክር ቤቱ የሚወጣው ደንብ የፍርድ ቤቶችን ልዩ የሥራ ጠባይ፣ እያንዳንዱ የስራ መደብ የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታና ልምድ፣ የሥራ መዘርዝሮችን ይዘትና ስፋት ሌሎች ተዛማጅ መመዘኛዎችን ታሳቢ በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፤
5) የአስተዳደር ሠራተኞች መብት እና ጥቅማ ጥቅም በመንግሥት ሠራተኞች

## 11. The Human Resource Administration of Regional Courts

1) The Regional Courts shall have the full right to recruit, employ, and administer its own administrative staff;
2) The Regional Supreme Court shall have full independence to employ or appoint administrative staffs by examining and designing the positions and levels necessary for the judicial process;
3) Recruitment, employment, placement, promotion, transfer, training, salary, benefits, disciplinary matters and other related cases of the Regional courts administrative staffs shall be determined by a regulation to be issued by the State Council;
4) The regulation to be issued in accordance with sub-article (3) shall be determined by the special nature of the courts, the required skills and experience of each position, the content and scope of the job details and other related criteria;
5) The rights and benefits of administrative staff shall not be less

ሕጎች ለሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ከተፈቀደው ሊያንስ አይችልም፤

6) የአስተዳደር ሠራተኞችን በተመለከተ የሚወጡ ሕጎች እና የሚተላለፉ ውሳኔዎች ሁሉ ከፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነጻነት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡

7) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 11 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በጀትና የሰዉ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ የሚመራ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት በክልል ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

12. ኦዲት

የክልል ፍርድ ቤቶች የሒሳብ መዝገብ እና የበጀት አጠቃቀም በክልል ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና ተያያዥ ጉዳዮች**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን**

13.መሠረቱ

ስለ ክልል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት

than those allowed for other public employees by the Public Servants laws;

6) All laws and decisions relating to administrative personnel shall be in accordance with the institutional independence of the courts;

7) Without prejudice to the provisions of Article 10 and Article 11 of this Proclamation, the powers and duties of the budget and human resource management Bench head of the Supreme Court shall be determined by the regulation to be issued by the State Council in accordance with sub article 3 of this article.

**12. Audit**

Accounts and budget of the Regional Courts shall be audited annually by the Regional Auditor General.

**Part Three**

**Jurisdiction and Related Matters of the Regional Courts**

**Sub-Section One**

**Jurisdiction of the Regional Courts**

**13. Principle**

**Common Jurisdiction of Regional Courts**

1. The Regional courts shall have Common

| | |
|---|---|
| ጉዳዮች የወል የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡- | Jurisdiction on the following matters:- |
| ሀ) የክልሉን ሕጎች መሠረት በማድረግ በሚቀርቡ በፍርድ ሊወሰኑ በሚገባቸው ማናቸውም ጉዳዮች፣ | a) any justiciable matters which may be submitted in accordance with the laws of the Region; |
| ለ) በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት በግልጽ ተለይቶ ለፌዴራሉ መንግስት ባልተሰጡ ማናቸውም ጉዳዮች | b) any case not explicitly assigned to the Federal Government by the Federal Constitution; |
| ሐ) የክልሉን ሕገ-መንግስት እና ሌሎች ሕጎችን መሰረት አድርገው በሚነሱ ጉዳዮች፣ | c) matters arising in accordance with the Constitution and law of the Region; |
| መ) በሥነ ሥርዓት ሕጎች ወይም በሌላ ሕግ መሰረት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጡና በክልሉ ውስጥ በተከሰቱ ጉዳዮች፣ | d) cases arising in the Region, in accordance with the codes of procedure or other law; |
| ሠ) በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት በውክልና ለክልሎች በተሰጡ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል፤ | e) Federal cases delegated to the Regions in the Federal Constitution; |
| 2. በሕገ-መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች ለባህል፣ ለኃይማኖት እና ለአስተዳደር አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ውስጥ የዳኝነት ሥልጣን የክልል ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፤ | 2. Notwithstanding to the jurisdiction provided to cultural, religious, and administrative bodies under the Constitution and other laws, and jurisdiction of the Federal Courts, Jurisdiction shall be vested only in the Region Courts; |
| 3. በክልል ውስጥ የዳኝነት ሥልጣንን ከክልል ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጣቸው ሌሎች አካላት | 3. No special or ad hoc court shall be established that shall not obey the rule of law that exercise jurisdiction in the Region |

ውጭ የሚያደርግ፣ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ማንኛውም ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፤

4. ክልል ፍርድ ቤት በሥልጣኑ ሥር የሚወድቅን ጉዳይ በዳኝነት በማየት ላይ እንዳለ ወይም ፍርድ ከሰጠ በኋላ፡-

ሀ) መደበኛ ነዋሪነቱ ከክልል ውጭ የሆነ ሰው በማንኛውም ሁኔታ ወደ ክርክሩ ቢገባ፣

ለ) ወይም ከመድኅን ውል ጋር በተያያዘ መድኅን ሰጭው በክርክሩ ውስጥ ቢገባ ጉዳዩ በዚሁ ፍርድ ቤት መታየቱ ይቀጥላል፡፡

**14.የጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን**

1. በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ሀ) አንድ ጉዳይ ከአንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተዛውሮ እንዲታይ የሚቀርብን ጉዳይ አይቶ መወሰን፣

ለ) አንድን ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በተለያዩ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሥር የሚገኙ የወረዳ ፍርድ ቤቶች ሥልጣናችን ነው ብለው በያዙት ወይም ሥልጣናችን

outside of the Regional Courts or other bodies vested with jurisdiction by law;

4. Where the Regional Court is considering a case that falls under its jurisdiction or after giving a judgment:-

a) If a person who is not a principal resident of the Region enters the dispute under any circumstances;

b) If the insurer is involved in the dispute over the insurance contract, the case shall be continued to be heard in this court.

**14. The Jurisdiction of the Supreme Court**

1) Notwithstanding to the jurisdiction given by other laws, the Supreme Court shall have first instance jurisdiction over the following cases:

a) To hear and decide over cases of Change of venue from one high court to the other or to itself;

b) To hear and decide a case, on a request for an appropriate order to be made, where two or more High Courts or Woreda Courts under different High Courts have held that it is within our

አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ጉዳዩን አይቶ መወሰን፤

**15.የጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን**

ሀ) የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሳኔ የሰጠበትን፣

ለ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠበትን፣እና

ሐ) በሌሎች ህጎች የተሰጡ ጉዳዮችን በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው፤

**16.የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን**

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሚቀርቡለትን እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች በሰበር የማየት እና የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው፡-

ሀ) በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የተሰጠበትን ማናቸውንም ጉዳይ፣

ለ) በክልል ዳኝነት ስልጣኑ መነሻነት

jurisdiction or have ruled that it is not within our jurisdiction;

**15. Appellate Jurisdiction of the Supreme Court**

a) Decisions of the Regional High Court rendered in its first instance jurisdiction;

b) Decisions of the High Court rendered in its appellate jurisdiction in variation of the decisions of the Wereda or City Administration Court of First Instance; and

c) has appellate jurisdiction over cases provided for by other laws;

**16. Cassation Power of the Supreme Court**

The Regional Supreme Court of Cassation shall have jurisdiction to hear and decide on the following cases in which there is a fundamental error of law:-

a) Any case in which the final judgment, decision, ruling or order is given by the Wereda or city administration Court;

b) any case in which the final judgment,

በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የተሰጠበትን ማናቸውንም ጉዳይ፤

ሐ) በክልል ዳኝነት ስልጣኑ መነሻነት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ፍርድ፣ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የተሰጠበትን ማናቸውንም ጉዳይ፤

መ) በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በሌሎች አካላት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ፤

1) "መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት" ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት ያለበት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን፣ ትእዛዝ፣ ሆኖ፡-

ሀ) የክልልን ወይም የፌዴራሉን ሕገ-መንግሥት በመጣስ የተወሰነ ጉዳይ፣

ለ) ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ተፈጻሚነት ያለውን ሌላ ዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ የተወሰነ ጉዳይ፣

ሐ) ግልጽ የሆነ የሕግ ድንጋጌን ወይም የሕግ መርሕን በመጣስ የተወሰነ ጉዳይ፣

መ) ህግን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን

decision, ruling or order is given by the High Court on the basis of the Regional judicial jurisdiction;

c) any case in which the final judgment, decision, ruling or order is given by the Supreme Court on the basis of the regional judicial jurisdiction, and;

d) The final decision made by bodies authorized by law or other bodies;

1) "Fundamental error of law" shall be final judgment, decision, ruling, or order which may be filed in Region Supreme Court Cassation Bench that contains either one or similar of the following fundamental errors and finally distorting justice:

a) Decision in violation of the Regional or Federal constitution;

b) Decision in violation of international treaties ratified by Ethiopia or other applicable international law;

c) in violation of a clear Statute or principle of law;

d) misinterpretation of law or citing irrelevant law;

ሕግ በመጥቀስ የተወሰነ ጉዳይ፣

ሠ) ተገቢው ጭብጥ ሳይያዝ የተወሰነና ከፍ ያለ የፍትሕ መዛባት እንደሚያስከትል የታመነበት ጉዳይ፣

ረ) በዋናው ፍርድ ላይ ከተወሰነው ውጭ እንዲፈፀም የተወሰነ ጉዳይ፣

ሰ) ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ ጉዳይ፣

ሸ) ከሥልጣን ውጭ ወይም የመወሰን ሥልጣን ሳይኖር በአስተዳደር አካል ወይም ተቋም የተወሰነ ጉዳይ፣

ቀ) በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወይም በሰበር ፓናል ችሎት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመቃረን የተወሰነ ጉዳይ፣

በ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ሳለ ሊታይ አይገባም ተብሎ የተወሰነ ጉዳይ፤

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም ሲባል "የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ" ማለት በንዑስ አንቀጹ ከፊደል (ሀ) እስከ (መ) ድረስ በተዘረዘሩት አካላት የተሰጠ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ

e) by not framing the appropriate issue or by framing an issue irrelevant to the litigation;

f) in violation the decision of the main judgement;

g) a case in which there is no substantive of jurisdiction to hear the case;

h) A matter decided by an administrative body or institution outside its jurisdiction or without authority to decide.

i) A case decided in contrary to the binding legal interpretation given by the Federal Supreme Court Cassation Bench or Cassation Panel;

j) A case ruled as non justiciable while it is justiciable;

2) For the application of sub-article (1) of Article 14 of this Proclamation, "final judgment, decision, or order" means a judgment, decision, ruling or order that may not be appealed or completed of its process by the parties listed in sub-article (a to d);

ፍርድ፣ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ነው፤

3) አንድ የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ ሦስት ዳኞች የተሰየሙበት የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ያመነ እንደሆነ ነው፤

4) የጠቅላይ ፍርድ ቤት አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደአስፈላጊነቱ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል።

## 17.የሰበር አቤቱታ አቀራረብና የክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት

1) በሰበር እንዲታይ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሥርዓቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) አቤቱታ የሚያቀርበው ተከራካሪ ወገን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በአቤቱታው ውስጥ በዝርዝር ማቅረብ አለበት፤

ለ) አቤቱታ የቀረበበትን የበታች ፍርድ ቤቶች ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም

3) A final judgment, decision, ruling or order may be considered a fundamental error of law if the Supreme Court Cassation Inquiry Bench, in which three judges are appointed, admits that there is a fundamental error of law;

4) The Cassation Bench of five judges of the Supreme Court may in accordance with this Proclamation, affirm, amend, change, or revoke the appealed final judgment, decision, ruling, or order.

## 17. Cassation Complaint Submission and Dispute Administration Procedure

1) Any petition for cassation shall meet the following procedures:

a) The party to the complaint shall state in detail in the complaint reasons for the fundamental error of law;

b) A copy of the lower court's decision, judgment, ruling or order shall be

ትዕዛዝ ግልባጭ ከሰበር አቤቱታው ጋር ማያያዝ አለበት፤

2) የሰበር አቤቱታ የሚቀርበው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠ ወይም ይኸው በይፋ ከተነገረበት ዕለት ጀምሮ በሚታሰብ በዘጠና ቀናት ውስጥ ነው፤

3) የሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ በማጣራት፡-

ሀ) የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለመኖሩን ከተረዳ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ መዝገቡንም በመዝጋት አመልካቹን ያሰናብታል፣

ለ) የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ ከተረዳ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ጭብጥ በመያዝ መልስ እንዲሰጥበት የአመልካችን አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር ለተጠሪ ይልካል፤

4) የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰበር ተከራካሪዎች የጽሑፍ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተከራካሪዎችን አስተያየት ወይም የሕግ ሙግት መስማት ይችላል፡፡

attached to the cassation appeal;

2) A cassation appeal shall be sumbitted within ninety days from the date of the final judgment, decision, ruling or order of the case or from the date of its official announcement;

3) The Cassation Inquiry Bench shall examine the cassation appeal and investigate whether there is a fundamental error of law in the case:-

a) Where it considered that there is no fundamental error of law has been committed, shall reject the appeal and close the case and dismiss the applicant;

b) Where it recognized that there is a fundamental error of law, shall send a petition to the respondent with the summons requesting that the case be referred to a cassation hearing Bench;

4) When it deems necessary, the Cassation Court may hear the comments or legal arguments of the parties after the conclusion of the written argument.

## 18.የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ መርህ እና የአስተዳደር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙት ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ የመቀበልና የመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው፡-

ሀ) በሚንቀሳቀስ እና በማይንቀሳቀስ ንብረት ከብር ሦስት ሚሊዮን (3,000,000.00) በላይ የገንዘብ ግምት ያላቸውን ጉዳዮች፤

ለ) በክልል መንግሥት ውስጥ የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችን እና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች፤

ሐ) አንድ ጉዳይ ከአንድ የወረዳ ወይም የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ወረዳ ወይም የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ ተዛውሮ እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታን፤

መ) የወረዳ ወይም የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ በሚሰጠው ማናቸውም ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን እና ትዕዛዝ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታን፤

## 18. Jurisdiction of the High Court in Civil Matters

**1)** Notwithstanding to the general principles and administrative boundaries under Article 13 of this Proclamation, the High Courts with in the Region shall have matterial jurisdiction in the first instance to receive and adjudicate the following cases in civil matters:-

a) Movable and immovable property where the amount involved exceed Birr three million (3,000,000);

**b)** Disputes concerning businesses and associations registered or established in the Region;

**c)** An appeal of a case transferred from one Wereda court or first instance court to another Wereda court or high court or to the same court to be heard;

d) An appeal over any decision, judgement, verdict or order on the jurisdiction of the wereda or first instance Court; and

ሠ) በሌላ ሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርብን የይግባኝ አቤቱታ፤

2) በሌሎች በፌዴራልም ሆነ በክልል ሕጎች ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ሥልጣኖች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

19.የከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ መርሕ እና የአስተዳደር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ የመቀበልና የመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው፡-

1) በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን፤ ስረ-ነገር
2) በክልል ማናቸውም ሕጎች ውስጥ የተደነገጉ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንዲዳኙ የተለዩ የወንጀል ጉዳዮችን፤
3) አንድ የወንጀል ጉዳይ ከአንድ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ

e) Appeal to decisions made by other judicial bodies in accordance with the powers vested to them by other law;

2) The powers vested on regional high courts by other federal and regional laws remain working.

**19. Jurisdiction of the Criminal Cases of the High Court**

Notwithstanding to the general principles and administrative boundaries under Article 13 of this Proclamation, the High Courts in the Region shall have the matterial jurisdiction to receive and adjudicate the following cases in the first instance in criminal proceedings:-

1) Criminal cases that fall under the original jurisdiction of the Regional High Court in accordance with the Criminal Procedure Code and other relevant laws;
2) Criminal cases specified in any law with in the Region and subject to jurisdiction of the High Court;
3) An application for change of venue from one Wereda or city administration first

| | |
|---|---|
| ደረጃ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታን፤ | instance court to another or to its own high court; |
| 4) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ በሚሰጠው ማናቸውም ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን እና ትዕዛዝ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታን፤ | 4) An appeal against any judgment, decision, ruling, or order rendered by the woreda or City Administrative Court of First Instance in its first instance jurisdiction;; |
| 5) በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተመለከተ ሌሎች አካላት በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርብን የይግባኝ አቤቱታ፤ | 5) An appeal against a decision made by other bodies under their authority based on another law; |
| 6) የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ፍርድ ቤቶች መካከል የተከፋፈለ መሆኑን መሠረት በማድረግ የተወካዮች ምክር ቤት በፌዴራል የወንጀል ሕግ ከተካተቱት ወንጀሎች ውስጥ በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲዳኙ የለያቸውን የወንጀል ጉዳዮች። | 6) On the basis of the Bench of jurisdiction between the Federal and Regional Courts, the criminal cases that the House of peoples Representatives decided to be adjudicated under the jurisdiction of the Regional High Court. |
| **20. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን** | **20. First Instance Civil Jurisdiction of a Wereda or City Administration Court** |
| በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ስር የሰፈረው | Notwithstanding to the general principles and |

አጠቃላይ መርሕ እና የአስተዳደር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ውስጥ የሚገኙ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በፍትሐ-ብሔር ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች የመቀበልና የመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው፡-

1) በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች መሠረት በወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን፤
2) በፍትሐብሔር ጉዳይ በሚንቀሳቀስ እና በማይንቀሳቀስ ንብረት እስከ ብር 3,000,000 (ሦስት ሚሊዮን ብር) የሚደርስ የገንዘብ ግምት ያላቸውን ጉዳዮች፤
3) ተወላጅነት እና በገንዘብ የማይገመቱ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ አቤቱታ፤
4) በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር እንደሚወድቅ ያልተመለከተን ወይም ለሌላ የዳኝነት አካል ያልተሰጠን የፍትሐብሔር ጉዳይን፡፡

administrative boundaries under Article 13 of this Proclamation, Wereda or city administration courts with in the Region shall have matterial jurisdiction to receive and adjudicate the following cases in civil cases:-

1) civil cases that fall under material jurisdiction of a Wereda or city administration court in accordance with the Code of Civil Procedure and other relevant laws;
2) Civil cases of movable and immovable property where the amount involved does not exceed Birr (3,000,000) three million;
3) application regarding filiation as well as matters the value of which cannot be expressed in money;
4) A civil matter that shall not be considered or falling or that shall not be subjected to jurisdiction of the Region High Court or Supreme Court.

## 21. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ መርሕ እና የአስተዳደር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ውስጥ የሚገኙ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች የመቀበል እና የመዳኘት የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡-

1) በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የፌደራል ሕጎች መሠረት በክልል መንግስት የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንደሚወድቁ የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮችን፤
2) በክልል ማንኛውም ሕጎች ውስጥ የተደነገጉ እና በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር እንዲዳኙ የተለዩ የወንጀል ጉዳዮችን፤
3) የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል እና በክልል መንግሥት ፍርድ ቤቶች መካከል የተከፋፈለ መሆኑን መሠረት በማድረግ የፌደራል ተወካዮች ምክር ቤት የወንጀል ሕግ ከተካተቱት ወንጀሎች ውስጥ በክልል

## 21. First Instance Criminal Jurisdiction of Wereda or City Court

Notwithstanding to the general principle and administrative boundaries under Article 13 of this Proclamation, Wereda or City Administration Courts with in the Region shall have matterial jurisdiction to recieve and adjudicate the following criminal matters:-

1) Criminal matters falling under matterial jurisdiction of the wereda or city administration courts within the Regional State in accordance with the Code of Criminal Procedure and other relevant Federal laws;
2) Criminal matters provided in any of the laws of the Region and specified to be adjudicated under the jurisdiction of the Wereda or City Administration Court;
3) The jurisdiction, on the basis of the Bench of jurisdiction between the Federal and Regional State Courts, the criminal matter that the House of Peoples Representatives decide to be adjudicated under the jurisdiction of

ወረዳ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲዳኙ የለያቸውን የወንጀል ጉዳዮች፡፡

the Wereda Courts of the Region.

### 22.የክልል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው መሠረታዊ ሕጎች

የክልል ፍርድ ቤቶች በባለጉዳዮች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ክርክሮችን በተመለከተ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሕጎች ተከትለው ዳኝነት ይሰጣሉ፡-

1) የፌደራልና የክልል ሕገ-መንግሥት፤
2) ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፤
3) በኢትዮጵያ ተፈጻሚነት ያላቸው ዓለም አቀፍ የልማድ ሕጎች፤
4) በሥራ ላይ ያሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የሕግ ማስታወቂያዎች፤

### 22. Substantive laws applicable to the Regional Courts

The Regional courts shall adjudicate the petitions and disputes submitted by the applicants on the basis of the following substantive laws, as may be relevant:-

1) Federal and Regional Constitution;
2) International agreements accepted and ratified by Ethiopia;
3) International customary law applicable to Ethiopia;
4) Proclamations, regulations , directives, and legal notices currently in effect;

### 23.የክልል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕጎች

የክልል ፍርድ ቤቶች በባለጉዳዮች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ክርክሮችን በተመለከተ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕጎች ተከትለው ዳኝነት ይሰጣሉ፡-

1) በሥራ ላይ ያሉ የወንጀል እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርኣት ሕጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 23. Procedure and Law of Evidence of the Regional Courts

Regional courts shall adjudicate on petitions and disputes filed by litigants, as applicable, in accordance with the following procedural and evidentiary rules:-

1) The existing criminal and civil procedural laws shall apply to the extent that they are not inconsistent with this Proclamation, as well as other relevant laws, to matters not covered by this Proclamation.

2) በክልል ምክር ቤት እንዲሁም በሌሎች ሥልጣን ባላቸው አካላት የወጡ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ጉዳይን የሚመለከቱ ሕጎችን ወይም ድንጋጌዎችን፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**የፍርድ ቤቶች ችሎትና ተያያዥ ጉዳዮች**

**24.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች**

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የፍትሐብሔር ጉዳይ ችሎት፣

ለ) የወንጀል ጉዳይ ችሎት፣

ሐ) የሰበር አጣሪ ችሎት፣

መ) የሰበር ሰሚ ችሎት፤

2) ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳይ አይነት የተለዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጅ ይችላል፤

3) በጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ፣ የወንጀል ይግባኝ እና የሰበር አጣሪ ችሎት ላይ አንድ ሰብሳቢ ዳኛ እና ሁለት ዳኞች ይሰየማሉ፤

4) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ ሰብሳቢ ዳኛ እና አራት ዳኞች ይሰየማሉ፤

5) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በየትኛውም የጠቅላይ

2) Laws or regulations issued by the State Council and other competent bodies concerning matters of procedure and evidence.

**Sub-Section Two**

**Courts Bench and Related Matters**

**24. Supreme Court Benchs**

1) The Regional Supreme Court shall have the following Benchs:-

a) Civil Bench;

b) Criminal Bench;

c) Cassation Inquiry Bench,

d) Cassation Hearing Bench;

2) The Supreme Court may, when it deems necessary, organize additional Benchs on specified cases;

3) One presiding judge and two judges shall be appointed at the Supreme Court in civil appeal, criminal appeal and cassation inquiry Bench;

4) The Supreme Court's cassation bench shall consist of one presiding judge and four judges;

5) The President or Vice President of the Supreme Court may preside over any of

ፍርድ ቤት ችሎት ላይ ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ መስማትና መወሰን ሥራ ሂደት ባለቤት የሆነ ዳኛ በማንኛውም ችሎት ዳኛ ሲጓደል ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፤

**25. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎቶች**

1) በክልል ውስጥ የተደራጀ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) የፍትሐብሔር ጉዳይ ችሎት፣

   ለ) የወንጀል ጉዳይ ችሎት ይኖሩታል፡፡

2) የትኛውም ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳይ አይነት የተለዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጅ ይችላል፤

3) በከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት አንድ ሰብሳቢ ዳኛ እና ሌሎች ሁለት ዳኞች ይሰየማሉ፤

4) የብርበራ ትዕዛዝ፣የመያዣ ትዕዛዝ፣ የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ በአንድ ዳኛ የሚታይ ሆኖ የዋስትና ጥያቄ ሲቀርብ በሶስት ዳኛ መታየት አለበት፤

5) የፍትሐብሔር እና የወንጀል ይግባኝ ጉዳዮች የጉዳዩ ክብደትና ውስብስብነት ካላስገደደ በቀር በአንድ ዳኛ ሊታዩ ይችላሉ፤

the hearings of the Supreme Court.

6) Without prejudice to sub-article 5 of this Article, a judge who coordinates complaint hearing and decision core process at the Supreme Court may be appointed as a presiding judge in the absence of a judge;

**25. High Court Benchs**

1) The High Court organized in the Region shall have the following Benchs:-

   a) Civil Bench;

   b) Criminal Bench;

2) The Supreme Court may, when deemed necessary, arrange additional Benchs on specified cases;

3) In the High Court Bench, one presiding judge and two other judges shall be appointed;

4) The orders of search, arrest warrant, and remand shall be heared by one judge and a bail application shall heared by three judges;

5) Civil and criminal appeals may be heard by a single judge unless the gravity and complexity of the case dictates it;

6) ማንኛውም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ባለበት ፍርድ ቤት በየትኛውም ችሎት ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ መስማትና መወሰን ሥራ ሂደት አስተባባሪ የሆነ ዳኛ በማንኛውም ችሎት ሲጓደል ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፤

### 26.የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቶች

1) እያንዳንዱ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአንድ ዳኛ የሚያስችል ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ችሎቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የፍትሐብሔር ጉዳይ ችሎት፣
   ለ) የወንጀል ጉዳይ ችሎት፣
   ሐ) የቤተሰብ ጉዳይ ችሎት፣
   መ) የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ችሎት፤

2) የትኛውም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳይ አይነት የተለዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጅ ይችላል፡፡

6) The President or Vice President of any High Court may be appointed as presiding judge of any Bench of the High Court.

7) Without prejudice to sub-article 6 of this Article, a judge who coordinates the process of complaint hearing and decision core process in the High Court may be appointed as a presiding judge in absence of a judge;

### 26. Wereda or City Administration Court Benches

1) Each Wereda or City Administration Court shall make trial by one first instance judge shall have the following Benchs:-
   a) Civil Bench;
   b) Criminal Bench;
   c) Family Bench;
   d) Employer and labour Bench;

2) Any Wereda or City Administration first instance court may organize additional hearings on specific cases as it deemed it is necessary.

## ክፍል አራት

## የዳኞችና የፕሬዝዳንቶች አሿሿም፣ሥልጣንና ተግባር

### ንኡስ ክፍል አንድ

### የዳኞችና የፕሬዝዳንቶች አሿሿም

### 27.የዳኞች ምልመላ እና አሿሿም

1) የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በዋና ጉባዔ አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት ይሾማሉ፤

2) ዳኞችን በእጩነት መልምሎ ለሹመት ለማቅረብ የሚያገለግሉ መስፈርቶች በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

### 28.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት አሿሿም

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት በክልል ርዕሰ-መስተዳድር አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት ይሾማሉ፤

2) የክልል ርዕሰ-መስተዳድር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንትን እና ምክትል ፕሬዚደንትን ለሹመት በሚመርጥበት ጊዜ እጩዎቹ፡-

## Part Four

## Appointment, Powers and Functions of Judges and Presidents

### Sub-section One

### Appointment of Judges and Presidents

### 27. Recruitment and Appointment of Judges

1) Judges of the Supreme Court, High Court and the Wereda or City Administration Courts shall be appointed by the State Council up on the recommendation of the Judicial Administration Council;

2) The criteria for recruiting candidate judges for nomination shall be in accordance with the Regional Judicial Administartion Proclamtion.

### 28. Appointment of the President and Vice-President of the Supreme Court

1) The President and Vice-Presidents of the Region Supreme Court shall be appointed by the State Council up on the recommendation of the Chief Executive of the Region;

2) When the Chief Executive of the Region nominates the President and Vice-Presidents of the Supreme Court, the candidates shall :-

ሀ) በሕግ ሙያ የዳበረ ልምድ እና የላቀ የሙያ ብቃት ያላቸው መሆኑን፤

ለ) ከፍተኛ የሕግ እውቀት እና መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆኑን፤

ሐ) የፍርድ ቤቶችን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል የአመራር ብቃት ያላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**29.የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች አሿሿም**

1) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፤ ምክትል ፕሬዚደንት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚደንቶች በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቅራቢነት በየምክር ቤቶቻቸው ይሾማሉ፤

2) የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚደንቶች ለማሾም በሚመርጥበት ጊዜ እጩዎቹ፡-

ሀ) በሕግ ሙያ የዳበረ ልምድ እና የላቀ የሙያ ብቃት ያላቸው መሆኑን፤

ለ) ከፍተኛ የሕግ እውቀት እና መልካም

a) have developed experience and professional qualifications in the legal profession;

b) have a high level of legal knowledge and good code of conduct,

c) take into account that they have the leadership skills to achieve the objectives and mission of the Courts.

**29. Appointment of the President, Vice President of the High Court, and Presidents of the Wereda or City Administration Court**

1) President and Vice President of the High Court and presidents of Woreda or City Administration Courts shall be appointed by their respective Council up on the recommendation of Zonal Chief Administrator;

2) When the Chief Administrator of the Zone nominate a President and Vice President of the High Court, Wereda or City Administration Court, the candidates shall have:-

a) developed experience and professional qualifications in the legal profession;

b) a high level of legal knowledge and

ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆኑን፤

ሐ)የፍርድ ቤቶችን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል የአመራር ብቃት ያላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**30.ቃለ መሐላ**

1) ፕሬዚደንቶች እና ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ከዚህ በታች የተመለከተውን ቃለ መሐላ መፈጸም አለባቸው፡-

"እኔ አቶ/ወ/ሮ/ ………… በዛሬው ዕለት የ ------ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት/ ምክትል ፕሬዚደንት/ ዳኛ ሆኜ ስሾም ለሕገ-መንግሥቱ ታማኝ በመሆን ከክልሉ እና ከሕዝቡ የተጣለብኝን ኃላፊነት በቅንነት፤ በታታሪነት እንዲሁም ሕግንና ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ሥራዬን ለመፈፀም ቃል እገባለሁ"፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ሥር የሰፈረው ቃለ-መሐላ አፈፃፀም የሚከናወነው በሚከተሉት አካላት ፊት በመቅረብ ይሆናል፡-

ሀ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት እና በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዳኞች በክልሉ ምክር ቤት ፊት፣

ለ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ

good code of conduct,

c) take into account that they have the leadership skills to achieve the objectives and mission of the Courts.

**30. Oath**

1) Prior to assuming their duties, Presidents and judge shall take the following oath:

***"I, Mr./Mrs. . . . today, when I am appointed as the President/Vice President/Judge of ------- Court, I sincerely fulfill the responsibility given to me by the state and the people being faithful to the Constitution; I promise to do my job diligently and in accordance with law and order";***

2) The execution of the oath under sub-article (1) shall be carried out in the presence of the following bodies:-

a) The President and Vice President of the Supreme Court, and the judges appointed by the courts at all levels infront of the State Council;

b) The Presidents of the High Court and Woreda or City

ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች በዞን ምክር ቤት ፊት ቀርበው ቃለ-መሐላ ይፈጽማሉ፡፡

### ንኡስ ክፍል ሁለት
### የፕሬዚደንቶች እና የምክትል ፕሬዚደንቶች ሥልጣንና ተግባር

**31.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሥልጣንና ተግባር**

1) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በሕግ መሰረት የክልሉን ፍርድ ቤቶች ለማስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፤
2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) የክልሉን ፍርድ ቤቶች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤

ለ) የክልሉን ፍርድ ቤቶች ዓመታዊ ሪፖርት፣ የስራ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ በጀቱንም ያስተዳድራል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የፍርድ ቤቶች የአፈፃፀም ሪፖርት ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በየሩብ ዓመቱ ይልካል እንዲሁም በዓመት ሁለት ጊዜ ያቀርባል፤

Administration Court shall take the oath infront of Zonal Council.

### Sub-section Two
### Powers and Functions of Presidents and Vice-Presidents

**31. Powers and Functions of the President of the Supreme Court**

1) The President of the Supreme Court of the Region shall have full legal power and responsibility to administer the Courts of the Region;
2) Notwithstanding to the general principles under sub-article (1), President of the Supreme Court shall have the following detail powers and functions:-

a) Principally manages, supervises, and administers the Courts of the Region;

b) Prepares annual report, work plan and budget of the Supreme Court and submits it to the State Council for approval; administer the budget, and implements the same;

c) Sends Courts performance report to the Standing Committee of the Council every quarter and presents twice a year;

መ) የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የተመደበላቸው በጀት ለሥራው በቂ መሆኑን ይከታተላል፣ የፀደቀላቸው በጀት ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

ሠ) የክልሉን የዳኝነት አገልግሎት ፖሊሲ እና ስልት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ረ) ለሹመት በዕጩነት የሚቀርቡ ዳኞችን እና የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ ተሿሚዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ለሹመት ያቀርባል፤

ሰ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት የችሎት ሰብሳቢ ዳኞችን ይመድባል፣ ዳኞችን በየችሎት ይደለድላል፤ዝርዝር የአፈፃፀም መስፈርቱ በመመሪያ ይወሰናል፤

ሸ) በየደረጃው ያሉ ዳኞች በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጹ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበለትን የመዋቅር ጥናት ተመልክቶ ይወስናል፣ አስፈላጊ የሆኑ የአስተዳደር ሠራተኞችን የሥራ መደብ እና ደረጃ ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት ቅጥር እንዲፈጸም ያደርጋል፤

d) Manages the sufficiency of the budget assigned to the high courts of the zone, wereda or city administration first instance courts, and ensures that the approved budget is implemented;

e) Prepares the policy and strategy of the judicial service of the Region and follows its implementation;

f) Submits candid Judges and Judicial Council nominees for appointment by concerned bodies;

g) Appoint the presiding judges of Supreme Court Benchs and deploy judges at each Bench; details shall be determined by directives;

h) Follows-up and verifies judges good code of conducts;

i) Looks and determines the structure proposal presented in accordance with sub-article 3 of Article 12 of this Proclamation; decides on position and job rank and make the necessary staff to be hired;

| | |
|---|---|
| በ) የፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ወጪ ቆጣቢ፣ ተደራሽ፣ ተገማች እና ለህዝብ ግልጽ የሚሆንበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ አዳዲስ የአሠራር ሥልቶችን እንዲቀየሱ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ | j) Establish a cost-effective, accessible, predictable and transparent system of court service delivery, develop and implement new procedures to be effective; follow-up its implementation; |
| ተ) የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር እና ለማሻሻል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት ይሠራል፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር መልካም ተሞክሮዎችን ይዳስሳል፣ የክልል ዳኞች የተሻለ ልምድ የሚቀስሙበትን እና በየጊዜው ራሳቸውን በዕውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት የሚገነቡበትን ስልት በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ | k) Work closely with stakeholders to strengthen and improve the judiciary service; explore local and foreign best practices, and create a conducive environment for the judges to learn best practices and build on their own knowledge, skills, and attitudes; |
| ቸ) በክልል ውስጥ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ድጋፍ ያደርጋል፤ | l) Support Sharia courts in the Region to carry out their judicial functions; |
| ነ) ዳኞች፣ የጉባኤ ተሿሚዎች እና የሌሎች የአስተዳደር ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ | m) Facilitate access to education and training for judges, appointees of judicial administration and other administrative staff; |
| ኘ) የዳኝነት ሥራ ለማጠናከር የሚረዱ የምርምር ሥራዎች እንዲደረጉ እና የዓመቱ ፍርዶች፣ ውሣኔዎች ተመርጠው በሕግ መጽሄት እንዲታተሙ ያደርጋል፤ | n) Make researches to be conducted and selected judgments and decisions be publish in a legal journal to strengthen the judicial service; |

ለ) ለፍርድ ቤቶቹ ሥራ የበለጠ መሻሻልና በአጠቃላይ ፍርድ ቤቶች ለኅብረተሰቡ የሚሰጡትን የፍትሕ አገልግሎት ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ረቂቆች በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመተባበር እንዲዘጋጁ እና ለክልል ምክር ቤት ቀርበው እንዲጸድቁ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነታቸውንም ይከታተላል፤

ኸ) የክልሉ ፍርድ ቤቶች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ፈጣን የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

ወ) በክልል ፍርድ ቤቶች ፕሮግራሞችና የሥራ ዕቅዶች ውስጥ የሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች ስለመካተታቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

ዘ) ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ይወክላል፤

ዠ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ጉዳይ በውክልና ለሚሠሩ ፍርድ ቤቶች ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የበጀት ማካካሻ ይጠይቃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

የ) በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

o) In order to further improve the work of the courts and to strengthen the judicial service, in collaboration with concerned organs make a draft laws be prepared and submitted to the State Council for approval; follow-up its implementation;

p) Make the Regional courts provide fast judicial services supported by information technology;

q) Follows-up and verifies the mainstreaming of gender issues in regional court programs and action plans;

r) Represent the Supreme Court in dealings with third parties;

s) Requests budget compensation from the Federal Supreme Court for the courts looking federal matters by delegation and up on its approval, effects to be implemented;

t) Performs other functions provided to it in this Proclamation and other laws.

## 32.የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ሥልጣንና ተግባር

1) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ፕሬዚደንቱ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እና ሁኔታ ተክቶ ይሠራል፤

2) በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ መርሕ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክትል ፕሬዚደንት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) የዳኝነት አገልግሎት ዘርፉን የሥራ እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ጉድለት ባጋጠመ ጊዜም ከፕሬዚደንቱ ጋር በመመካከር ተገቢውን የእርምት እና የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

ለ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት የአቤቱታ መስማትና መወሰን ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ፣ የምድብ ችሎት አስተባባሪዎችን፣ ችሎት ሰብሳቢ ዳኞችን፣ ሌሎች ዳኞችን እና የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ተሿሚዎችን ስራ ያቀናጃል፣ ያስተባብራል፣

ሐ) ከዳኝነት አገልግሎት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የሕግ ረቂቆች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ሲጸድቁም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

## 32. Powers and functions of the Vice President of the Supreme Court

1) The Vice-President of the Supreme Court shall acts on behalf of the President in his absence or in his incapability to work;

2) Notwithstanding to the general principle under sub-article(1), the Vice President shall have the following detail powers and functions:-

a) closely follow-up the Judiciary service; provide appropriate support; and take appropriate corrective action in consultation with the President when fault occurs;

b) Coordinate and organize the works Hearing and judgement Core Process owner, Bench Coordinators, Presiding Judges, other Judges and Judicial Council Appointees;

c) Make draft legislation to be prepared in relation to Judicial Service and follow-up their implementation upon approval;

መ) የዳኝነት አገልግሎትን ለማሻሻል የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደርን ይከታተላል፣

ሠ) በፕሬዚደንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**33.የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሥልጣንና ተግባራት**

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ተጠሪነቱ ለዞን ምክር ቤትና ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በሥሩ የሚገኙ ፍርድ ቤቶችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች የተሰጣቸውን ተግባር በትክክል ማከናወናቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣ እንደአስፈላጊነቱም ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤
3) የንዑስ ጉባዔ ተሿሚዎችን በእጩነት ያቀርባል፤
4) አስፈላጊ የሆኑ የፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ሠራተኞችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፤
5) ለዋና ጉባኤ እና ለንዑስ ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ

d) Follow-ups the case flow management to improve the judicial service;

e) Perform such other duties assigned specifically to him by the President.

**33. Powers and functions of the President of the High Court**

The President of the High Court is accountable to Zonal Council and the Regional Supreme Court and shall have the following detail powers and functions:-

1) Heads, administers, follow ups and supervises the works of the courts under it;
2) Follow-ups the functions of the President of the Wereda or City Administration Court; supervise, verify, and provide the necessary support as may be necessary;
3) Submit candids of Judicial administration sub-council to appointment;
4) employ and administer the Administrative Staffs in accordance with applicable law;
5) Notwithstanding the powers and functions

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የምድብ ችሎት አስተባባሪዎችን፣ አቤቱታ መስማትና መወሰን ዋና ሥራ ሂደት አስተባባሪዎችን፣ የንኡስ ጉባዔ ተሿሚዎችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤

vested in the Judicial Administration Council and Judicial administration sub-council, heads, supervises and administers the high Court Bench Coordinators, Chief Coordinator of hearing and judgement, Judicial administration sub-council Appointees;

6) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የፍርድ ቤቱን ዳኞች በየችሎቱ ይደለድላል፣ ሰብሳቢ ዳኞችን ይመድባል፣ በዳኞች የዓመት እረፍት ጊዜ ተረኛ ችሎት ዳኛ ወይም ዳኞችን ይመድባል፤

6) According to the directive issued by the Supreme Court of the region, assigns presiding judges and other judges to each Bench, assign judges to the benches during judges annual leave;

7) የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን፣ በሥሩ የሚገኝ ወረዳና የከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለዞን ምክር ቤት አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

7) Prepare the work plan and budget of the High Court, Wereda and city administration courts under it, submit it to Zonal Council for approval and implement the same up on approval;

8) የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን፣ የወረዳና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን የሥራ አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለዞኑ ምክር ቤት ይልካል፤ በዓመት ሁለት ጊዜ ሪፖርቱን ለምክር ቤት ያቀርባል፤

8) Quarterly Submits the High Court and Woreda or City Administration court report to the Supreme Court and Zonal Council and presents twice a year;

9) በፍርድ ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ወጪ ቆጣቢ፣ ተደራሽ፣ ተገማችና ለህዝብ ግልጽ የሚሆኑበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ስለተፈጻሚነቱም ክትትል

9) Establish and follows the implementation of cost-effective, accessible, predictable and transparent system of services in the court;

ያደርጋል፤

10) በስሩ የታቀፉ ፍርድ ቤቶች የሥራ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ አዳዲስ የአሠራር ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

11) አስተማሪነት ያላቸው የአመቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔዎች ተመርጠው ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲላኩ ያደርጋል፤

12) የዳኝነት ሥራውን ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይሠራል፤

13) በዋና ጉባዔው፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ እና ምክትል ፕሬዚደንት የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

14) በሕገ-መንግሥትና በዚህ አዋጅ የተደነገገውን በማይቃረን ሁኔታ በሌሎች ሕጎች መሠረት የተሰጡ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 34.የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ሥልጣንና ተግባር

1) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ፕሬዚደንቱ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

10) Develops and follows the implementation of new procedures to ensure the efficiency and effectiveness of the courts under it;

11) Make sure that the decisions of the High Court with educative value in the Year be sent to the Supreme Court ;

12) Works in consultation with the concerned bodies to strengthen the works of judiciary;

13) Implement decisions and directives conveyed by the Judicial Administration Council, the President and the Vice-Presidents of the Supreme Court;

14) Performs duties in accordance with other laws, without prejudice to the provisions of the Constitution and this proclamation.

## 34. Powers and functions of the Vice President of the High Court

1) The Vice-President of the High Court shall act on his behalf when the President is absent or incapable to perform his duties;
2) Notwithstanding to the general

2) የንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክትል ፕሬዚደንቱ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ)አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የአስተዳደር ሠራተኞችን ያስተዳድራል፣

ለ) የአስተዳደር ዘርፉን የሥራ እንቅስቃሴ ውጤታማነት በቅርብ ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

ሐ) ከአስተዳደር ሥራዎች እና ሠራተኞች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሕጎች አፈጻጸም ይከታተላል፣

መ) የአስተዳደር ዘርፉን ሰራተኞች የትምህርት እና የስልጠና ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሠ) የአስተዳደር ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የተቀየሱ ስልቶችን ተፈፃሚ ያደርጋል፣ አፈጻጸም ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ጉድለት ባጋጠመ ጊዜ ከፕሬዚደንቱ ጋር በመመካከር የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

ረ) በፕሬዚደንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**35.የወረዳ ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሥልጣንና**

provisions of sub-article (1), the Vice President shall have the following detail powers and functions:-

a) Administer the administrative Staffs in accordance with the appropriate law;

b) Closely follows the performance of the administrative Bench and provide appropriate support;

c) Follows the implementation of laws related to administrative duties and administrative staffs;

d) Facilitate the education and training of the administrative staffs;

e) Follows the implementation of reform activities; provide appropriate support, and take corrective measures in consultation with the President in case of limitations;

f) Performs such other duties granted specifically to him by the President.

**35. Powers and functions of the President of the Wereda or City Administration First Instance Court**

The President of the Woreda or City

ተግባር

የወረዳ ወይም የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ተጠሪነቱ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

1) ፍርድ ቤቱን ያስተዳድራል፣ ይወክላል፣
2) በሥሩ የሚገኙ ዳኞችን፣ አቤቱታ መስማትና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችን የሥራ ሁኔታ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣
3) ዳኞችን በየችሎቱ ይደለድላል፣ በዳኞች ዓመት እረፍት ጊዜ ለተረኛ ችሎት ዳኞችን ይመድባል፣
4) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የአስተዳደር ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፤
5) የፍርድ ቤቱን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በጀቱን ያስተዳድራል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤
6) የፍርድ ቤቱን የሥራ አፈፃፀም ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ አዳዲስ የአሠራር ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ያረጋግጣል፤
7) የፍርድ ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ ለወረዳው ምክር ቤትና ለከፍተኛ ፍርድ

Administration First Instance Court is accountable to the High Court and shall have the following detail powers and functions:-

1) Administers and represents the court;
2) Follow-up, supervise, and administer the working conditions of judges, complaint hearing and decision core process coordinators under it;
3) Deploy and assign judges at each Bench and during judges' annual leave;
4) Recruit, deploy and administer the necessary adminstrative staff in accordance with the relevant law;
5) Prepares the work plan and budget of the court, submits it to the High Court; administers the budget upon approval;
6) Develop and validate new procedures to assist the court in its efficient and effective process;
7) Sends a quarterly report of the work to the wereda Council and the High

ቤት በየሩብ ዓመት ሪፖርት ይልካል፤ የአፈፃፀም ሪፖርት በዓመት ሁለት ጊዜ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

8) እንደአግባብነቱ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት እንዲሁም በዋና ጉባዔና በንዑስ ጉባዔ የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

9) በወረዳው ውስጥ የዳኝነት ሥራን ለማጠናከር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይሠራል፤

10) ከህገ መንግሥት እና ከዚህ አዋጅ ጋር በማይቃረን ሁኔታ በሌሎች ሕጎች መሠረት የሚሰጡ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ከኃላፊነት የሚነሱበት ሁኔታ

### 36. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት ከኃላፊነት የሚነሱበት አግባብ

1) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ከኃላፊነት ሊነሳ የሚችለው፡-

ሀ) በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ ሲወስን፤

ለ) በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል

Court; and presents two wice a year;

8) Appropriately implement decisions and directives issued by the President and Vice-Presidents of the Regional Supreme Court, the President and Vice-President of the High Court, as well as by the Judicial Administration Council and sub-councils;

9) works in collaboration with the concerned bodies to strengthen the judiciary;

10) Performs such other activities as may be provided in accordance with the Constitution and other laws.

## Part Five

## Termination of the Tenure of the Presidents and Vice-Presidents of the Courts

### 36. Condition for the Termination of the Tenure of the President, Vice-President of the Supreme Court

1) The President or Vice-President of the Supreme Court may terminate his duties when:-

a) he decides to resign voluntarily,

b) ensured as his violation makes failure to discharge his duties; or

c) it is believed that he manifests

ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤

ሐ) በአመራር ጉልህ ድክመት ማሳየቱ ሲታመን፤

መ) በሕመም ምክንያት ወይም በጡረታ፤

ሠ) የሹመት ግዜውን ከጨረሰ ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡፡

2) የክልል ርዕሰ-መስተዳድር የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል ጥፋት ፈጽሞ ወይም የአመራር ድክመት አሳይቶ መገኘቱን የተረዳ እንደሆነ፡-

ሀ) ከኃላፊነት ይነሳ ዘንድ ዝርዝር ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ለ) ምክር ቤቱ በርዕሰ-መስተዳድሩ የቀረበለትን ዝርዝር ሪፖርት መርምሮ በአብላጫ ድምፅ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤

3) የክልል ርዕሰ-መስተዳድር የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል ከባድ ጥፋት መፈጸሙን የተረዳ እንደሆነ እና የፕሬዚደንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚደንቱ በኃላፊነት መቆየት ያልተፈለገ ውጤትን እንደሚያስከትል ካመነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጉባዔ

incompetence;

d) Due to illness and retirement.

e) He may be removed from his duty after completing his term of office.

2) when the President of the Region recognizes that the president or vice-president of the Supreme Court has committed any offence or he is incapable of properly discharging his duties:

a) Prepare a detail report and submit it to the Council for his removal;

b) The State Council shall review the detail report submitted to it by the President of the Region and make appropriate decision by majority vote;

3) When the President of the Region realizes that the president or vice-president of the Supreme Court has committed a serious misconduct and that the stay in charge of the president or vice-president may result in unintended consequences, he may suspend him until a meeting of the Coincil is called;

ስብሰባ እስከሚጠራ ድረስ ለጊዜው ከኃላፊነት አግዶ ማቆየት ይችላል፤

4) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በራሱ ፈቃድ ኃላፊነቱን ለመልቀቅ የወሰነ እንደሆነ ኃላፊነቱን ከመልቀቁ ሶስት ወራት አስቀድሞ ለርዕሰ-መስተዳድሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፣ ርዕሰ መስተዳድሩም ጽሑፉ በደረሰው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕገ-መንግሥታዊ አሠራርን በመከተል ለፍርድ ቤቱ ጊዚያዊ ኃላፊ ከፍርድ ቤቱ ዳኞች መካከል በመመደብ መልቀቂያውን ይሰጠዋል፤

5) በራሱ ፈቃድ ኃላፊነቱን የለቀቀም ሆነ በአመራር ጉልህ ድክመት በማሳየቱ ምክንያት ከኃላፊነቱ የተነሳ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች በዳኝነት ተመድቦ ከመሥራት አይከለከልም፤

6) የሥነ- ምግባር ግድፈት በመፈጸሙ ምክንያት ከኃላፊነት እንዲነሳ የተደረገ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት የፈጸመው የሥነ-ምግባር ግድፈት በዳኝነት ሥራ ለመቀጠል የማያስችል መሆኑን በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተወስኖ ምክር ቤቱ ካላፀደቀ በስተቀር በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች በዳኝነት ተመድቦ

4) When the President or Vice-President of the Supreme Court decides to resign voluntarily, he shall notify to the President of the Region in writing three months prior to his resignation; within three months of receiving the letter, the president of the Region shall, in accordance with the constitutional order, appoint an interim head among the judges of the court and remove former;

5) The President or Vice-President shall not be prohibited from serving as a judge in the Supreme Court as a result of his voluntary resignation or dismissal due to manifest incompetence;

6) The President or Vice-President, who has been removed from his discharge as a result of misconduct, shall not be barred from sitting in the Supreme Court as a judge unless otherwise the Judicial Council decision approved by State Council in the violation disallows him from discharging his duties;

7) The details of the removal or

ከመሥራት አይከለከልም፤

7) በንዑስ አንቀጽ (5) እና በንዑስ አንቀጽ (6) በተደነገገው አግባብ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ችሎቶች ተመድቦ ሊሰራ የሚችል ከኃላፊነት የለቀቀ ወይም እንዲነሳ የተደረገ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ዝርዝር የአመዳደብ ጉዳይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

**37.የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች ከኃላፊነት የሚነሱበት ሁኔታ፡-**

1) ማንኛውም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት፣ ምክትል ፕሬዚደንት ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ከኃላፊነት ሊነሳ የሚችለው፡-

ሀ) በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ ሲወስን፤

ለ) በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤

ሐ)በአመራር ጉልህ ድክመት ማሳየቱ ሲታመን፤

መ) በሕመም ምክንያት ወይም በጡረታ፤

ሠ) የሹመት ግዜውን ከጨረሰ ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል።

termination of the President or Vice-President, which may be assigned to the Supreme Court Benchs in accordance with the provisions of sub-article (5) and sub-article (6), shall be determined by a directive to be issued by the Regional Supreme Court;

37. **Condition for Termination of Tenure of the president, vice-president of the High Court, presidents of wereda or city administration courts :-**

1) Any President or Vice-President of the high court or President of the Wereda or City Administration Court may be removed from office when:-

a) he decides to resign voluntarily,

b) it is confirmed that he has committed a misconduct making him incapable of properly discharging his duties;

c) it is believed that he has shown incompetence or inefficiency;

d) Due to illness and retirement;

e) He may be removed from his duty after completing his term of office.

2) where zonal administration shall determine whether the president or vice-president of the High Court or the

2) የዞኑ ዋና አስተዳደር በንዑስ አንቀጽ(1) እንደተደነገገው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል ጥፋት ፈጽሞ ወይም በአመራር ጉልህ ድክመት አሳይቶ መገኘቱን የተረዳ እንደሆነ፡-

ሀ) ከኃላፊነት ይነሳ ዘንድ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ለ) ምክር ቤቱም ጥፋት ስለመፈጸሙ ወይም ጉልህ የአመራር ድክመት ስለማሳየቱ የቀረበለትን ሪፖርት መርምሮ በአብላጫ ድምፅ ሲፀድቅ ውሳኔ ይሰጣል፤

3) በንዑስ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እንደተደነገገው የዞኑ ዋና አስተዳደር አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት በኃላፊነት ለመቀጠል የማያስችል ከባድ ጥፋት መፈጸሙን የተረዳ እንደሆነ እና የፕሬዚደንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚደንቱ በኃላፊነት መቆየት ያልተፈለገ ውጤትን እንደሚያስከትል ካመነ እስከ ተከታዩ የምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ ድረስ ከኃላፊነት አግዶ ማቆየት ይችላል፤

president of the Wereda or City Administration court has committed any offence or manifests incompetence, as provided in sub-article (1):-

a) prepares a detail report for the dismissal from his discharge and submits it to the Zonal Council;

b) The Council shall, after examining the report of the misconduct, manifests incompetence, make the appropriate decision;

3) Notwithstanding to sub-article (2), when the zonal administration recognizes that a president or vice-president or Wereda or City administration court president has committed a serious offense that does not allow him to remain in his discharge and that the resignation of the president or vice president will result in unintended consequences, it may suspend his discharge until the meeting time of the Zonal Council;

4) President or Vice-President removed from his discharge on the basis of his own free will or manifests

4) በራሱ ፈቃድ ወይም በአመራር ጉልህ ድክመት በማሳየቱ ከኃላፊነቱ የለቀቀ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት በሚገኝበት እርከን ፍርድ ቤት ችሎቶች በዳኝነት ተመድቦ ከመሥራት አይከለከልም፤

5) የሥነ-ምግባር ግድፈት በመፈጸሙ ምክንያት ከኃላፊነት እንዲነሳ የተደረገ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት የፈጸመው የሥነ-ምግባር ግድፈት በዳኝነት ሥራ ለመቀጠል የማያስችል መሆኑ እንደአግባብነቱ በዋና ጉባኤ ወይም በንዑስ ጉባዔው ካልተወሰነ በስተቀር ዳኛ ሆኖ ከመመደብ አይከለከልም፤

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ዝርዝር የአመዳደብ መመሪያ የሚፈፀም ይሆናል፤

7) ኃላፊነቱን በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ የወሰነ ማንኛውም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ኃላፊነቱን ከመልቀቁ 3 ወራት አስቀድሞ እንደአግባቡ ለዞኑ ወይም ለወረዳ ዋና

incompetence, shall not be barred from being a judge in the court;

5) President or Vice-President who is removed as a result of misconduct shall not preclude him from being appointed as a judge unless deemed appropriate by the Judicial Administration Council or the Judicial administration sub-council;

6) The provisions of sub-paragraphs (4) and (5) will be implemented according to the detailed assigning directives issued by the Supreme Court of the Region in accordance with sub-article 7 of Article 37 of this Proclamation;

7) Any President, Vice-President or Wereda or City Administration Court President who decides to resign voluntarily his discharge shall inform in writing to the zonal or woreda or City administration 3 months prior to his resignation; following this, the court adopts an interim judge and removes him, and concerning Chief Administration of the case shall, within three months receiving in the

አስተዳደር በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ዋና አስተዳደር ጽሁፉ በደረሰው በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ህጋዊ አሠራር በመከተል ለፍርድ ቤቱ ጊዜያዊ ኃላፊ ከፍርድ ቤቱ ዳኞች መካከል በመመደብ መልቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ከዳኝነት ሥራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችና የዳኝነት ሥራ አመራር ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ከዳኝነት ሥራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

**38.የማስቻያ ስፍራ**

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ የማስቻያ ስፍራ ሳውላ ከተማ ነው፤
2) የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች መደበኛ የማስቻያ ቦታ የየዞኑ ዋና ከተማ ነው፤
3) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ቦታ የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ዋና ከተማ ነው፤
4) በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሚያቋቁሙት ምድብ ችሎት ማስቻያ ቦታ ምድብ ችሎቱ በሚቋቋምበት ከተማ ይሆናል፤
5) በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4)

writing, appoint the interim head of the court in accordance with due process.

## Part Six

## Issues related to judicial activity and powers and duties of judicial management officials

### Sub Section One

### Matters related to the work of the judiciary

**38. Place of sitting**

1) The Regular Place of sitting of the Region Supreme Court shall be in Sawla City;
2) The regular place of seat of the High Court shall be the capital town of each Zone;
3) The Regular place of sitting of the Woreda or City Administration First Instance Courts shall be the capital town of the Woreda or City Administration;
4) The Bench bench sitting shall be shall be the city where the Bench bench is established;
5) Notwithstanding to the provisions of sub-article (1-4), courts at any level may

የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ውጤታማ ለማድረግ ተዘዋዋሪ ችሎት ሊያደራጅ ይችላል፡፡

## 39.በግልጽ ችሎት ማስቻል

1) የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን በግልጽ ችሎት ማከናወን አለባቸው፤
2) ፍርድ ቤቶች የችሎት የክርክር ሂደትን ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለሕዝብ እና ለመገናኛ ብዙኃን ክፍት ማድረግ አለባቸው፣ ይህን አስመልክቶ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤
3) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (1) እስከ (2) ያሉ ድንጋጌዎችና ለዳኝነት አሠራር አግባብ ያላቸው የሥነ-ሥርዓት ሕጎች የሚደነግጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቶች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ጉዳዮችን በዝግ ችሎት ሊያዩ ይችላሉ፡-

ሀ) ለተከራካሪዎች የግል ሕይወት፣

ለ) ለሕዝብና ለመንግሥት ደህንነት፣

ሐ) ለምስክሮች ደህንነት፣

መ)ለመልካም ጠባይ ወይም ለግብረ-ገብነት

convene a circuit bench to make the judicial service more efficient, cost-effective and accessible to the public.

## 39. Open Hearing

1) The regional courts shall discharge their judicial proceedings in an open court;
2) Courts have a duty to make an open proceedings in addressing the disputing parties, public and mass media; the Supreme Court may issue detail implementation guidelines in this regard;
3) Notwithstanding to the provisions of sub-article (1-3) and the relevant rules of procedure for judicial proceedings, the courts may hear cases in camera for one or more of the following grounnds:-

a) the right to privacy of the disputing parties concerned;
b) For the people and government safety;
c) For the safety of witnesses;
d) When necessary for good conduct or morality, or
e) When juvenile are accused or present as witnesses.

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ሠ)ሕጻናት ተከሰው ወይም ምስክሮች ሆነው ሲቀርቡ።

40.የሥራ ቋንቋ

1) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋ የክልሉ መንግስት የስራ ቋንቋ የሆነው አማርኛ ነው፤

2) የከፍተኛ፣ የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ በዞን ምክር ቤት ሊወሰን ይችላል፤

3) ፍርድ ቤቶች የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ መናገር ለማይችል ተከራካሪ ወገን ብቃት ያለው አስተርጓሚ መመደብ እና ከውሳኔ በኋላም በይግባኝ ግዜ ውሳኔውን ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉሞ መስጠት አለባቸው።

41.የዳኞች ከችሎት መነሣት

1) የማንኛውም ፍርድ ቤት ዳኛ ቀጥሎ ከተመለከቱት ጉዳዮች በአንዱ ምክንያት ከችሎት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፣

ለ) ከተከራካሪዎቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ተወካይ በሆነበት ጉዳይ ላይ ክርክር የተነሳ

**40. Working Language**

1) Amharic,the working language of the Region, shall be the working Languge of the Supreme Court;

2) The working language of the High, Woreda and City Administration First Instance Courts may be determined by Zonal Council;

3) Courts shall have a duty to assign a qualified interpreter to the party who does not speak the working language of the court and after the decision they must translate the decision and give the Amharic version during an appeal.

**41. Withdrawal of a Judge**

1) Any judge shall be removed from his bench on account of one of the following grounds where:-

a) he has relation with one of the disputing parties or the advocate thereof by consanguinity or by affinity;

b) the dispute relates to a case for whom

እንደሆነ፣

ሐ) ክርክር የተነሣበት ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት፣ በግልግል ዳኝነት፣ በዕርቅ ያየው ሆኖ ከተገኘ፤ ሆኖም አግባብ ባለው የሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ቀድሞ ወደ ወሰነው ፍርድ ቤት በመመለስ ሂደት ጉዳዩ የተመራለት ዳኛ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፤

መ) ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ፣ ወይም

ሠ) ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጥም የሚያሰኝ ማንኛውም ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር ሊነሳ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን ሲያውቅ ሌላ ዳኛ እንዲተካ የችሎት ዳኛ ለሚደለድለው ኃላፊ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 42.ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት

1) ከተከራካሪዎች አንደኛው በአንቀጽ 41 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ዳኛ ከችሎት መነሳት ያለበት እንደሆነ ይህንኑ በሚመለከት ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፤

he acts or acted as tutor, legal representative or advocate to one of the disputing parties;

c) he has previously acted as judge or mediator or an arbitrator in connection with the case or the subject matter of the dispute; however, this shall not apply to the case redirected by the appellate court to be entertained by the court that previously decided as per relevant procedural law;

d) he has a case pending in court with one of the parties or the advocate thereof; or

e) When there is any other sufficient reason to believe that justice may not be served.

2) The judge concerned shall notice to the court to be replaced by other judge and withdraw as soon as he is aware of the existence of conditions in Sub-Article (1) of this Article.

## 42. Application for Removal of a Judge

1) Where one of the party to a case find out that a judge should not sit for one of the reasons specified in Article 41 of this

2) ማመልከቻው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፤

3) ዳኛው ብቻውን የሚያስችል ሆኖ ከችሎት ስለመነሳት የቀረበውን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄውን የተቀበለ እንደሆነ ከችሎት ይነሳል፤

4) ዳኛው ከችሎት ስለመነሳት የቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበለ እንደሆነ በዚያው ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፣ ሌላ ችሎት ከሌለ የዚሁኑ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ይተላለፋል፤

5) ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበለት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር የሚያስችል ከሆነ ማመልከቻው በዚያው ችሎት ካሉት ዳኞች በተጨማሪ ሌላ ዳኛ በመሰየም በአምስት ቀን ውስጥ መወሰን አለበት፤

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ ለሌላ ችሎት በደረሰ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ መወሰን አለበት፤

7) ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ነው፡፡

Proclamation, shall submit a written application to the court requesting the removal of the judge;

2) The application shall be made before the hearing or soon after the party becomes aware of the reason for making such an application;

3) Where a judge is sitting alone, he shall after considering the application, be withdrawn from looking the case when he accepts the request;

4) Where the judge does not accept the request to be withdrawn, a rule over the withdrawal shall be made by other bench of the court, or in the absence of other bench, the appellate court shall give a ruling;

5) Where the judge is sitting with other judges, the matter shall be decided by the other judges who sit in the same Bench. within five days;

6) A request submitted in accordance sub-article (4) shall be rendered within fifteen days from the date such application reached other Bench;

7) The decision over withdrawal of a judge shall be final with no appeal;

8) ዳኛው ከችሎት እንዲነሳ ከተወሰነ ውሳኔውን ወዲያውኑ መፈፀም አለበት፡፡

**43.ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሳራ እና ቅጣት**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 መሠረት የቀረበውን ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ተገቢ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ከቀረ የጉዳዩ ውጤት ግምት ውስጥ ሳይገባ ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው በዋናው ጉዳይ ተከራካሪ ለሆነው ለሌላኛው ወገን ኪሳራ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊወስንበት ይችላል፤

2) ዳኛው ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበው ያለ በቂ ምክንያት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ በአመልካቹ ላይ እስከ ብር 3,000 (ሦስት ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊወስንበት ይችላል፤

3) አቤቱታው የቀረበው ሆን ብሎ የዳኛውን ስም ለማጥፋት ወይም ክብር ለመጉዳት ወይም ጉዳዩን ለማጓተት መሆኑ በታወቀ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እስከ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) የሚደርስ መቀጮ እንዲከፍል ሊወስንበት ይችላል፡፡

**44.ጉዳይን ወደ ሌላ ስፍራ ስለማዛወር**

1. ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት

8) The Decision given on withdrawal of a judge shall be executed forthwith.

**43. Cost and Penalty of Application for Removal of a Judge**

1) Where the application submitted in accordance with Article 42 of this Proclamation is dismissed, the court may order the costs of the other disputed party be borne by the applicant irrespective of the outcome of the main case;

2) Where a party makes an application without good cause, the court may, in addition to dismissing the application, impose a fine up to 3000 (three thousand) Birr;

3) Provided however, the applicant makes a malicious application with the intention of defaming or damaging judges honor or delaying the proceedings, the court may impose a fine of up to Birr 5,000 (five thousand birr).

**44. Change of Venue**

1) One of the disputing party may

ምክንያቶች አንዱን ወይም ሌላውን በመጥቀስ ጉዳዩ ተመሳሳይ የሥረ-ነገር ሥልጣን ወዳለው ሌላ ፍርድ ቤት ወይም የይዛወርልኝ ጥያቄውን እየተመለከተ ወዳለው የበላይ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይለት ለበላይ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡

ሀ) ጉዳዩን ማየት የጀመረው የበታች ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያለአድልዎ በትክክል ለማስተናገድ የማይችል መሆኑን፣

ለ) ጉዳዩ ዘወትር የማያጋጥም እና አስቸጋሪ የሕግ ክርክር የሚያስነሳ መሆኑን፣ ወይም

ሐ) በተጠየቀው መሠረት ወደ ሌላ ስፍራ መዛወሩ ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለምስክሮቹ ምቹ መሆኑን ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ ፍርድ ለማስገኘት የሚያስችል መሆኑን፤

2. የይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበለት የበላይ ፍርድ ቤት በቀረበው አቤቱታ ላይ ሌላኛው ባለጉዳይ አስተያየት እንዲያቀርብ ካደረገ በኂላ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ቢያንስ አንዱ የተሟላ ሆኖ ካገኘው ጉዳዩን እየታየ ካለበት ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ተመሳሳይ እርከን ላይ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ራሱ ተዛውሮ እንዲታይ ሊወስን ይችላል፤

3. ጉዳይ ይዘዋወርልኝ ጥያቄን በመቀበል

apply for a higher court for a change of venue a case to be seen by other courts having matterial jurisdiction or by the higher court itself based on the following grounds:-

a) The lower court, which has begun hearing the case, is unable to fairly handle;

b) where in the case raised a legal dispute of unusual difficulty, or

c) where a change of veneu makes it convenient for disputing parties or witnesses and for delivering justice in a short period of time;

2) The Supreme Court to which the transfer request was made may, after hearing the other party on the petition, if at least one of the reasons listed in sub-article (1) is met, the court may decide to transfer the case to another court of the same jurisdiction or to itself;

3) An appeal may not be made over a

ወይም ውድቅ በማድረግ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም፤

4. የጉዳይ ይዛወርልኝ ጥያቄን ያስተናገደ ማንኛውም ፍርድ ቤት የቀረበለትን አቤቱታ ውድቅ ሲያደርግ በሌላኛው ተከራካሪ ወገን የደረሰን ወጭና ኪሳራ የይዘዋወርልኝ ጥያቄ አቅራቢው ወገን እንዲከፍል ሊወስን ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የዳኝነት ሥራ አመራር ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር

### 45. የአቤቱታ መስማት እና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሥልጣንና ተግባር

አቤቱታ መስማት እና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተለው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

1) የሥራ ሂደቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
2) ተጠሪ ለሆነለት አካል የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤
3) ለስራ ሂደቱ የሚመደብለትን ዓመታዊ በጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ያደርጋል፤
4) በጉዳዮች መለኪያ ወይም ስታንዳርድ መሠረት በሥሩ ለሚገኝ የሥራ ክፍል የሥራ ስምሪት ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

decision given on change of venue;

4) A court that ruled out a change of venue application may order the applicant to cover the costs incurred by the other party.

## Subsection Two

## Powers and Functions of the Judiciary Administartion Heads

### 45. Powers and Duties of Hearing and Judgement Process Coordinator

Hearing and Judgement Process Coordinator is accountable to the President of the Court and shall have the following detail powers and functions:-

1) Prepares plans of the process; follows-up its implementation;
2) Submits a performance report to the body of which it is accountable for;
3) Makes the annual budget allocated for its intended use;
4) Provides work order to the units in accordance with the standards set, and follows-up its implementation;

5) የሥራ ሂደቱን ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

6) ጠንካራና ደካማ አፈፃፀሞችን በመለየት ችግር ፈቺ በሆኑ ሀሳቦች ላይ የስራ ሂደቱን አባላት ያወያያል፣ መፍትሔ ይሰጣል፤

7) የመዝገቦችን ብዛት እና የጉዳዮችን ፍሰት እያጠና የተሻለ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ለምክትል ፕሬዚደንቱ ሃሳብ ያቀርባል፤

8) በሥሩ በሚገኙ ችሎቶች የሚያስችሉ ዳኞች ተሟልተው ማስቻላቸውንና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ጉድለት በታየ ጊዜም ከምክትል ፕሬዚደንቱ ጋር በመመካከር ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፤

9) ከመዛግብት ጋር በተያያዘና የስራ ሂደቱን በሚመለከት በባለጉዳዮች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ መፍትሔ ይሰጣል፤

10) የስራ ሂደቱን አባላት የሥነ-ምግባር ሁኔታ ይከታተላል፣ የሚታዩ ጉድለቶችንም በመለየት የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ እንደአጥፊው ማንነት ለንኡስ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት

5) Principally coordinates and supports the activities of the Process;

6) Discusses with the process members on problem-solving ideas by identifying strong and weak performance; recommend solutions;

7) Recommend to the Vice President that a better system to be put in place by studying the task load and case flows;

8) Follow-up, supervise and ensure that the judges in the courts meet their obligations and carry out their duties properly, and in the event of any deficiencies, consult with the Vice-President and take corrective action;

9) Receives and resolves customer complaints regarding cases and over the working unit;

10) Follow-up the ethics of members of its process; identifies noticeable deficiencies and takes corrective action; as per the law submits to human resource

ወይም ለአስተዳደር ሠራተኞች የሰው ሐብት አስተዳደር ያቀርባል፤

11) በፕሬዚደንቱ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

12) በዞን፤ በወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የአቤቱታ መስማት እና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ተጠሪነት ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት ሆኖ እንደአግባብነቱ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**46. የምድብ ችሎት አስተባባሪ ሥልጣንና ተግባር**

1) በጠቅላይ ፍርድ ቤትና በየእርከኑ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚቋቋሙ ምድብ ችሎቶች የራሳቸው አስተባባሪ ይኖራቸዋል፤

2) የምድብ ችሎት አስተባባሪ ተጠሪነት ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት ሆኖ በአንቀጽ 46 የተመለከተውን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡፡

**47.የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ሥልጣንና ተግባር**

በሌላ ሕግ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የሚሰየምበትን ችሎት፡-

1) በበላይነት ይመራል፣

management or judicial administration sub-council for diciplinìary measure;

11) Performs such other related duties provided by the President;

12) Complaint Hearing and Dicision Process Coordinator of the Zonal, and Woreda or City Administration Courts shall be accountable to the President of the Court and shall perform the duties pursuant to this Article as may be appropriate.

**46. Powers and functions of the Bench Bench Coordinator**

1) Bench benches to be established by the Supreme Court and the courts at all levels shall have their own coordinator;

2) The Coordinator of Bench bench shall be accountable to the President of the Court and shall perform the functions pursuant to Article 46.

**47. Powers and Functions of the Presiding Judge**

Notwithstanding to the powers and functions vested to him by other law, the presiding judge shall:-

1) Principally manages the bench he

2) የስራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
3) የዳኞች አፈጻጸም በጉዳዮች መለኪያ ወይም ስታንዳርድ መሠረት መሆኑን ይከታተላል፣
4) የችሎት መዛግብት አቀጣጠርና ክፍፍል በተገቢው ሥርዓት እየተመራ ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፣
5) በችሎት በሚታዩ መዛግብት ላይ የሚደረግ ውይይትን በአግባቡ ይመራል፣ በሁሉም የችሎቱ ዳኞች ግንዛቤ የተወሰደባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
6) ዳኞች በችሎት የሚሰጡ ፍርዶችን፣ ውሳኔዎችን፣ ብይኖችንና ትዕዛዞችን በማዘጋጀት ሂደት ተመጣጣኝ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤
7) ጠንካራ እና ደካማ አፈፃፀሞችን በመለየት ችግር ፈቺ በሆኑ ሀሳቦች ላይ ከችሎት ዳኞች ጋር በመወያየት መፍትሔ ይሰጣል፤
8) የመዝገቦችን ብዛት እና ፍሰት እየተከታተለ የተሻለ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ለመስማትና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሃሳብ ያቀርባል፤
9) ችሎቱ በተሟላ ዳኛ መካሄዱንና ዳኞች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ባጋጠመ ጊዜም

presides;

2) Prepares a work plan and follow-ups its implementation;
3) Follows-up as the performance of judges is in accordance with the criteria or standards set;
4) Supervise the compilation and distribution of court cases;
5) Leads discussions on court cases and ensures that all judges are informed;
6) Supervises the fair participation of judges in the preparation of verdicts, decisions, judgments and orders;
7) Identifies strong and weak performance and discusses problem-solving ideas with judges and provides solutions;
8) Recommend to the Complaint Hearing and Decision Process Coordinator to follow-up the number and flow of cases and establish a better system;
9) Ensures and supervises that the entire trial is conducted by a judge and that the judges fulfill their responsibilities,

ከመስማትና መወሰን የስራ ሂደት አስተባባሪ ወይም ከምድብ ችሎት አስተባባሪ ጋር በመመካከር ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

10) በችሎቱ ከሚታዩ መዛግብት በተያያዘና ችሎቱን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ አስፈላጊውን የተፋጠነ ምላሽ ይሰጣል ወይም ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

**48.የዋና ሬጅስትራር እና የሬጅስትራር ሥልጣን እና ተግባር**

1) ዋና ሬጅስትራር ተጠሪነቱ እንደአግባቡ ለሚመለከተው የአቤቱታ መስማትና መወሰን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ወይም ለምድብ ችሎት አስተባባሪ ሆኖ በሌላ ሕግ ከተደነገገው በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የክፍሉን ሥራ በማቀድ ይመራል፣ ያደራጃል፣ የማስተባበርና የቁጥጥር ስራን በመስራት ያስተዳድራል፣

ለ) የስራ ድጋፍና ግምገማ፣ የውጤት ምዘና ያካሄዳል፣ ለክፍሉ ስራ አስፈላጊ የሆነ አቅርቦት እንዲሟላ ያደርጋል፣ የእቅድ አፈፃፀም የስራ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሐ) የችሎት አስተዳደር ሥራዎች በየዕለቱ

and shall, in consultation with the Compliant Hearing and Decision Core Process Coordinator or the Bench Coordinator, take appropriate corrective action to be taken in the case of failure;

10) Receives complaints from the court cases and other cases relating to the proceedings; responds as soon as necessary or submits the case to the relevant body;

**48. Powers and Functions of the Chief Registrar and Registrar**

1) In addition to those provided for in this Proclamation and other laws, the Chief Registrar shall be accountable to the Complaint Hearing and Decision Process Coordinator or Bench bench Coordinator and shall have the following powers and functions፡-

a) Manages and administers the works of the department by planning, organizing, coordinating, and supervising.

b) Performs job assessment and evaluation; provides the necessary supplies; and submits work plan and performance reports;

መከናወናቸውን ይከታተላል፣ የአሠራር ክፍተት ሲኖር ለሚመለከተው አስተባባሪ ያሳውቃል፣

መ) ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የችሎት አስተዳደር ሥራ እንዲኖር ከሚመለከተው አስተባባሪ ጋር በመነጋገር የተሻለ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሠ) ጉዳዩ ከሚመለከተው አስተባባሪ ጋር በመመካከር የቀጠሮ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፣

ረ) በሚመለከተው የአቤቱታ መስማት እና መወሰን የሥራ ሂደት ወይም በምድብ ችሎት ለሚገኙ የሬጅስትራር ቡድን መሪዎች የሥራ ስምሪት ይሰጣል፣ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ስለመወጣታቸው ይከታተላል፣ ጉድለት ሲኖር ከሚመለከተው አስተባባሪ ጋር በመመካከር ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ሰ)በስሩ በሚገኙ ሬጅስትራሮችና የሬጅስትራር ቡድን መሪዎች ወይም ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ጉድለት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አስተባባሪ ያቀርባል፣

ሸ)ለሥራው የሚያስፈልጉ የሬጅስትራር

c) Follow-up the day-to-day works of court proceedings and informs to the relevant coordinator when there is a procedural gap;

d) Ensures better and more effective court administration work with the relevant coordinator;

e) Works the appointment policy shall be implemented in consultation with the concerned coordinator;

f) Gives work order with relevant Hearing and Decision Core Process or Bench bench; follow-up performance of their responsibilities, and takes appropriate corrective action in consultation with the relevant coordinator in case of failure;

g) Submits to the appropriate coordinator for the disciplinary action against the misconduct of the

ሠራተኞች እንዲሟሉ ለሚመለከተው አስተባባሪ ያሳውቃል፣

ቀ) ለጉዳዮች ፍሰት አመራርና አስተዳደር ተግባራዊነት የሚጠበቅበትን ይሠራል፣

በ) በክፍሉ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከባለጉዳዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል ምላሽ እንዲያገኙ ይሠራል፣

ተ) በፕሬዚደንቱ፣ በምክትል ፕሬዚደንትና ጉዳዩ በሚመለከተው አስተባባሪ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

2) የፍርድ ቤቱ ምክትል ሬጅስትራር ተጠሪነቱ ለዋና ሬጅስትራር ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) በፍትሐብሔርና በወንጀል የሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በሌሎች ሕግጋት ለሬጅስትራር የተሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፣

ለ) ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በስነ-ስርዓት ሕጎች የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው የተዘጋጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ) ለአከፋፈት እንዲያመች የተጠየቀውን ዳኝነት በመለየት ጉዳዩን ወደ ሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፣ ፋይሎች እንዲከፈቱ ይመራል፣

መ) የችሎት መዛግብት በቀጠሮ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣

registrars and registrar team leaders or employees under him;

h) Notifies to the relevant coordinator so that the required registrar staff to be fulfilled;

i) Works for the implementation and flow of case management and administration requirements;

j) Receive complaints from clients on the provision services and respond to them;

k) Performs other duties assigned by the President, Vice President and the relevant coordinator;

2) The vice Registrar of the Court shall be accountable to the Chief Registrar and perform the following duties:-

a) Performs functions assigned to the registrar in civil and criminal procedure and other laws;

b) Ensures applications submitted to the court are prepared in accordance with the requirements of the Code of procedure;

c) Identify the court case required for distribution and transfer the case to the relevant unit, directs

ሠ) በዳኛ የተሰጡ ትዕዛዞችን በማረጋገጥ ፈርሞ ወጪ ያደርጋል፣

ረ) በተንቀሳቃሽና በተዘጉ መዝገቦች ዙሪያ ለሚቀርቡ አግባብ ለሆኑ ጥያቄዎች መረጃዎችን ይሰጣል፣

ሰ) በዋና ሬጅስትራሩ የሚሰጡ የሥራ ክፍሉን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፣

ሸ) ዋና ሬጅስትራሩ በሌለ ጊዜ ተክቶ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**49.የተከላካይ ጠበቃ ጽ/ቤት ሥልጣን እና ተግባር**

የተከላካይ ጠበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ በየደረጃው ላሉት ፍርድ ቤቶች ፕሬዚደንት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1) በከባድ ወንጀል ተከሰው በራሳቸው ጠበቃ አቁመው የመከራከር አቅም ለሌላቸው ሰዎች ወይም በማናቸውም የወንጀል ጉዳይ ፍትህ ይጓደላል ተብሎ ሲታመን ተከሳሽን ይወክላል፤

2) የሕግ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ መልስ፣ አቤቱታዎችን፣ የይግባኝና የሰበር ቅሬታዎችን ያዘጋጃል፣ ክርክሮችን ያደርጋል፤

3) በማረሚያ ቤት በመገኘት ጥብቅና የቆመለትን ተከሳሽ ወይም ታራሚ ያማክራል፤

4) በመከላከያነት የሚያገለግል ደጋፊ ማስረጃ

the files to be opened;

d) Make the proceeding case to be provided by its appointment;

e) Signs and provide the judge's orders;

f) Provides information on relevant questions regarding dead and active files;

g) Performs additional duties assigned to him by the Chief Registrar.

h) Act on behalf of the Chief Registrar in his absence.

**49. Powers and Functions of the Office of Public Defender**

The public defender Office Head shall be accountable to the president of courts at all levels and shall have the following functions:-

1) Represent the defendant when it is deemed that miscarriage of justice may arise unless public defender is represented in the case where persons accused of a crime is unable to afford the cost of legal counsilor;

2) Provides legal aids; responds, prepares complaints, appeals and Cassation complaints; conducts debates;

3) Advise the Defendant or Prisoner in

ያሰባስባል፣ያደራጃል፤

5) የተከላካይ ጠበቆች ዝርዝር ተግባራት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**50. የጠቅላይ ፍርድ ቤት የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባራት**

የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለጉባዔዉና ፕሬዚደንቱ ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የክልል ፍርድ ቤቶች አስተዳደራዊ መዋቅር ተጠንቶ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር የአስተዳደር ሠራተኞችን ቅጥር ይፈጽማል፣ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣

ለ) የአስተዳደር ዘርፉን የሥራ ሂደቶች እንቅስቃሴና ውጤታማነት በቅርብ ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

ሐ) የአስተዳደር ሠራተኞችን የትምህርት እና የስልጠና ሁኔታ ያመቻቻል፣

መ) ከበጀት፣ ከመሠረተ ልማትና ሌሎች ሀብቶች እንዲሁም ከሰው ሀብት ጋር ግንኙነት ያላቸውንና በአጠቃላይ ዘርፉንና በዘርፉ ውስጥ ያለውን የአስተዳደር ሠራተኛ የሚመለከቱ ጥናቶች በማድረግ የውሳኔ ሐሳቦችንና

the Prison for whom he advocates;

4) Collect and organize supporting defense evidence;

5) The power and functions of the public defenders shall be determined by directive to be issued by Supreme Court.

**50. Powers and Functions of the head of Administration and Finance Bench of the Supreme Court**

The Administration and Finance Bench of the Region Supreme Court shall be accountable to the President and shall have detail powers and functions:

a) Make the administrative structure of the region courts to be approved by studying; appoints, employes, and administers administrative Staff in consultation with the President;

b) Follows-up closely the activities and efficiency of the administrative Bench and provide appropriate support;

c) Facilitate the education and training issues of the administrative Staff;

d) Submits resources to the President relating with budget, infrastructure, and other resources and draft laws, conducts research on resources related to human

ረቂቅ ሕጎችን እንዲዘጋጁ በማድረግ ለፕሬዚደንቱ ያቀርባል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሠ) የዘርፉን አሰራር ለመለወጥ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ጉድለት ባጋጠመ ጊዜ ከፕሬዚደንቱ ጋር በመመካከር የእርምት እና የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

ረ) በፕሬዚደንቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**ክፍል ሰባት**

**የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ**

**51.የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ መቋቋም**

በክልል ውስጥ ከዳኝነት ተግባር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮችና ሕግ-ነክ ጉዳዮችን በመለየት እንደ አግባቡ ለክልል ምክር ቤትና ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀሣብ የሚያቀርብ የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**52.የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ አባላት ስብጥር**

1. የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደን..ሰብሳቢ፣

ለ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት…ም/ሰብሳቢ፣

resources and Bench and administrative Staff under the Bench in general, and approves them when approved by the relevant body;

e) Follows-up the activities and implementation of reforms in the sector; provides appropriate supports, and takes measure and corrective action in consultation with the President in case of failure;

f) Performs such other duties granted specifically by the President.

**Part Seven**

**The Plenum of the Regional Courts**

**51. Establishment of the Plenum of the Regional Courts**

The Region Courts plenum is, hereby, established by this Proclamation to identify problems and legal issues related to the judiciary in the Region and to make recommendations to the Region council and the Supreme Court.

**52. The composition of the members of the Plenum of the Regional Courts**

1. Plenum of the Region Courts shall have the following members:-

a) President of the Supreme Court…

ሐ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት የአስተዳደር ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ….አባል፣

መ) የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች…አባላት፣

ሠ) የክልሉ ዳኞች ማኅበር ኃላፊ…… አባል፣

ረ) የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች …….አባላት፣

ሰ) የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባዔ አባል የሆኑ የከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ………..አባላት

ሽ) የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ………..አባል፣

ቀ) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የሚመደብ የጉባኤ ተሿሚ………..ፀሐፊ

2. የክልል ፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በዚህ ጉባዔ ላይ ይሳተፋል፤
3. በንዑስ አንቀጽ (1) ያልተጠቀሱ ዳኞች፣ የጉባዔ ተሿሚዎችና አግባብነት ያላቸው የክልሉን መንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ ማህበራት፣ ድርጅቶች፣ የሕግ

Chairperson;

b) Vice President of the Supreme Court…….vice chairperson;

c) Head of the Supreme Court Administration and Finance Bench…..Memeber;

d) Judges of the Supreme Court……members;

e) The head or representative of the Region Judges Association…member;

f) Presidents and Vice-Presidents of the High Court ………..Members;

g) High Court and wereda couerts judges who are members of the Region Judicial Administartion Judicial Administration Council ……….members;

h) Head of the Office of the Region Judicial Administration Judicial Administration Council …………….member;

i) Appointtee of the plenum assigned by the president of Supreme Court …….. Secretary;

2. The Head of the Region Justice Bureau

ትምህርት ቤቶችና የሳይንስ ተቋማት የሚወክሉ ሌሎች ሰዎች ድምጽ ሳይሰጡ እንዲሳተፉ በጉባዔው ሰብሳቢ አማካይነት ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡

**53.የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር**

የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ)በዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት፣ ተጠያቂነትና በክልሉ ባጋጠሙ የፍትሕ አስተዳደር ችግሮች ተወያይቶ መፍትሔ ይሰጣል፤

ለ) የዳኝነት አገልግሎት ለማሻሻል የሚረዱ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣ በተግባር ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል፤

ሐ) አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ ለክልል ምክር ቤት ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀሳብ ያቀርባል፣ የራሱን የሥራ ማስፈጸሚያ ውስጠ-ደንብ ያዘጋጃል፤

መ) የክልሉን የዳኝነት ሥራ ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

shall participate in this plenum without having the right to vote;

3. Judges not referred to under Sub-Article (1), representatives of appropriate government offices, associations, organizations, higher legal education institutions, or science institutions or other individuals may be invited by the chairperson of the plenum to participate in the Plenum without having the right to vote.

**53. Powers and Functions of the Plenum of the Regional Courts**

Plenum of the Regional Courts shall have the following powers and duties:

a) deliberate on problems encountered within the Region with respect to independence of the judiciary, accountability and administration of justice and grant remedies thereto;

b) Makes decisions that improve judicial services and ensures their implementation;

c) Proposes to the Region council or the Supreme Court the enactment of new laws or the amendment of existing laws; and shall prepare its own internal-regulations of procedures;

54.የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ የስብሰባ ጊዜ እና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

ሀ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ስብሰባዎችን ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ መደበኛ ስብሰባውን በዓመት አንድ ጊዜ ያካሂዳል፤

ለ) ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አባላት መካከል ሁለት-ሦስተኛው ሲገኙ ምልዓተ- ጉባዔ ይሆናል፤

ሐ) የክልል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ ገዢ ይሆናል፤

መ) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ጉባዔዉ የስብሰባ ጊዜ እና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

ክፍል ስምንት

ፍርድ ቤት መር አስማሚነት፣ መርሆዎች እና የአስማሚዎች ክፍያ

55.ፍርድ ቤት መር አስማሚነት

1) በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ከሚቀርቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ተመርጦ በፍርድ ቤቶች በሚቋቋም ፍርድ

d) Performs other related activities to facilitate and strengthen the judiciary in the region.

**54. Decision-Making and Meeting Time Procedure of the Region Courts Plenum**

a) Notwithstanding to the calling of extra-ordinary meetings as deemed necessary, the Region Courts plenum shall hold its regular meeting twice a year;

b) Two-thirds of the members of the Plenum those have the right to vote shall constitute a quorum;

c) Decisions shall be adopted by a majority vote; in case of equal vote, the chairperson shall have a casting vote.

d) Without prejudice to the provisions of this Article, the Plenum of Region Courts may prepare its own rules of procedure of meeting.

**Part Eight**

**Court Annexed Mediation, Principles and Cost of Mediators**

**55. Court Annexed Mediation**

1) Among the cases that are to be heard by the Wereda, City administration First Instance Court

ቤት መር አስማሚነት በኩል እንዲያልፍ ሊደረግ ይችላል፤

2) ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት መር አስማሚነት ጉዳያቸውን በስምምነት ካልጨረሱ በአስማሚዎች የተፈረመ ደብዳቤ ፍርድ ቤት በማቅረብ መደበኛ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ሊደረግ ይችላል፤

3) ተከራካሪዎች ስምምነት ላይ ከደረሱ የስምምነቱ ሁኔታዎች ግልጽ ሆኖ ከተለየና ተከራካሪዎቹ ከፈረሙበት በኋላ አስማሚው ሰነዱን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፤

4) ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ሰነድ በመመርመር ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን በማረጋገጥ ሊያጸድቀው ይችላል፣ የጸደቀው ስምምነትም እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥሮ ተፈጻሚነትን ያገኛል፤

5) በአንደኛው ተከራካሪ ወገን ያለመቅረብ ምክንያት የመስማማት ሂደቱ ካልተሳካ አስማሚው ይህንኑ በመግለጽ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፣ በድርድሩ ያልተገኘው ወገን ተገቢውን ክፍያ በመክፈል መደበኛ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ይደረጋል፤

and High Courts, mainly civil cases shall be referred through Court Annexed Mediation;

2) Where the parties have failed to resolve their dispute through Court Annexed mediation, the court proceedings may be initiated by filing a letter signed by the mediators to that effect;

3) Where the disputing parties to the agreement are clearly identified and the parties sign it, the mediator shall submit the document to the court;

4) The court may review the submitted document and approve the settlement agreement, stating that it is not contrary to the law and morals, the approved settlement agreement shall be executed like any decision of a court;

5) Where the proceeding is interrupted due to absence of the other party, the mediator shall report to the court by specifying the reason for the interruption and the court proceedings shall be initiated after the absency party paid appropriate

6) በፍርድ ቤት መር አስማሚነትም ሆነ በሌላ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግራ ቀኙ ከተስማሙ በህግ አግባብ ወጪ ተቀንሶ የዳኝነት ክፍያ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፤

7) ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ተግባራትን የሚያግዝና አስማሚዎችን የሚቆጣጠር የፍርድ ቤት አመራሮችን፣ ዳኞችንና የአስማሚነት ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

8) ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች አስመልክቶ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 56. በፍርድ ስለ አስማሚነት መርሆዎች

1) ፍርድ ቤት መር አስማሚነት የሚደረግ ማንኛውም ሂደት በእኩልነትና በባለጉዳዮቹ ሙሉ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ መሆን አለበት፤

2) በማስማማት ሂደቱ ተከራካሪ ወገኖች የሚሰጡት የእምነት ቃል ወይም ማንኛውም ንግግር ለፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብ አይችልም፣ ለዚህም አስማሚው ማረጋገጫ መስጠት አለበት፤

3) በፍርድ ቤት መር አስማሚነት በኩል

fee;

6) Where the parties have reached an agreement through court annexed mediation or other dispute resolving mechanism, any paid court fee shall be reimbursed after deducting mediation expenses by law;

7) The Supreme Court may establish a committee consisting of court leaders, judges and midition experts to assist and supervise the conduct of court-led mediation activities;

8) The Supreme Court may issue detail enforcement directives regarding the provisions of this Article.

## 56. Principles of mediation

1) The principle of mediation of the court shall be free and equal in any process of court annexed mediation;

2) The affidavit or any speech given by the disputing parties in the mediation process cannot be presented to the court as evidence, and the mediator shall provide proof of this;

የሚደረግ ማንኛውም የሃሳብ ልውውጥ ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ነው፡፡

**57.ስለ አስማሚዎች**

1) ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ከአምስት አመት ያላነሰ ጊዜ በህግ ሙያ ያገለገለ ሆኖ የአስማሚነት ስልጠና ወስዶ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚያወጣውን ምዘና ያለፈ ሰው አስማሚ ሆኖ ሊመረጥ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸውን የሚያሟላ ባለሙያጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያዘጋጀው የአስማሚዎች ሮስተር መዝገብ እንዲካተትሊደረግ ይችላል፤

3) ፍርድ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ብቁ አስማሚዎችን ሊቀጥር ይችላል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ከህግ ሙያ ውጭ በሆነ ሌላ ሙያ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ኤክስፐርቶችን የሙያቸውን አስፈላጊነት በመገምገም በአስማሚነት ሊቀጥር ይችላል፡፡

**58.ስለ ክፍያ**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 የተገለጹ አስማሚዎች አስተዳደራዊና ዓመታዊ ክፍያ ይከፍላሉ፤

3) Confidentiality of any communication through court annexed mediation shall be maintained.

**51. Mediators**

1) A person with a bachelor degree in law and with at least five years of experience in the field of law and who has taken training in mediation and has fulfilled the criteria set by the Supreme Court may be appointed as Mediator;

2) A professional who has fulfilled the requirements provided for in Sub-Article (1) of this Article shall be entered in the roster of mediators prepared by the Supreme Court;

3) The court may hire mediators as permanent or temporary employee as may be necessary;

4) Notwithstanding the provisions of sub-article (1), the court may employ experts with high experience in a profession other than the profession of law, in accordance with the assessment of the importance of their profession.

**58. Fee**

1) The Mediators mentioned under Article 57 shall pay annual and administrative fee;

2) አስማሚዎች በባለጉዳዮች ተመርጠው የማስማማት አገልግሎት ከሰጡ ተገቢው ክፍያ ይከፈላቸዋል፤

3) በማስማማቱ ሂደት የሚያልፉ ባለጉዳዮች ለፍርድ ቤት መር አስማሚነት ተገቢውን ክፍያ ይፈጽማሉ፤

4) የዚህ አንቀጽ የክፍያ ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 59.የክልል ፍርድ ቤቶች የሥራ ጊዜ

1) የክልል ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች የሥራ ሰዓት ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) ድንጋጌ ቢኖርም የክልል ፍርድ ቤቶች በየዓመቱ ከነሐሴ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ ዝግ ይሆናሉ፤

3) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በትርፍ ጊዜ በሚሰሩ ዳኞች ፍርድ ቤቶቹ ከሥራ ጊዜ ውጪ አስቸኳይ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ ሊደረግ ይችላል፤ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### 60. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር

የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸውን

2) Mediators who are elected by the parties and provides mediation service shall be entitled to appropriate fee for their service;

3) Parties to a court annexed mediation shall pay appropriate fee for the service;

4) Detail cases of fee referred to in this Article shall be determined by a directive to be issued by the Supreme Court.

## Part Nine
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 59. Working Hours Of Region Courts

1) The working hours of region courts and judges shall be the same as the working hours of other public offices;

2) Notwithstanding the provisions of sub-article 1), the Region Courts shall be closed from Nehase 1 to Meskerem 30 of each year;

3) Notwithstanding the provisions of this article, the courts may be made to deal with urgent cases outside of working hours by part-time judges; details shall be determined by the directives to be issued by the Supreme Court.

### 60. Administration of flow of cases

ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ወይም የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ሰሌዳ ገደብ በማስቀመጥ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ ቀልጣፋና ጥራቱ የሚረጋገጥበት የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ተግባራዊ ያደርጋሉ፤ዝርዝር አፈጻጸሙ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

The courts of the region implement case flow administration in which the justice delivery system is efficient and quality assured by setting a time limit for handling or completing the cases presented to them; detail implementation shall be determined by the directives to be issued by the Supreme Court.

**61.በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመዝገብ አመራር ሥርዓት ስለመዘርጋት**

1) የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ጉዳይ ክርክሮችን አዳዲስ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዲጂታል ወይም አዉቶሜትድ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ሥርዓት ሊዘረጉ ይችላሉ፤

2) ተከራካሪ ወገኖች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ክርክሮቻቸውን የማካሄድ ግዴታ አለባቸው፣ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**61. Technology Based File Management System**

1) Region courts may establish a system for digital or automated processing of civil or criminal case arguments using new information technologies;

2) Disputing Parties shall have the obligation to conduct their litigation by using the system; detail shall be determined by a directive to be issued by the Supreme Court.

**62.የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች**

1) በማንኛውም የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔና ትዕዛዝ በህግ እስካልተለወጠ ድረስ የፀና ሆኖ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ተፈፃሚ ይሆናል፤

2) በማንኛውም ክልል የሚገኝ የመንግስት አካል፣ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ

**62. Decisions and Orders of the Courts**

1) Unless otherwise provided by law, decisions or orders of the Region Courts shall be executed within the Region of Ethiopia;

2) Any government body or institution, non-

ድርጅት ወይም ማንኛውም ሰው ውሳኔዎቹን ወይም ትዕዛዞቹን የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

government organization or person residing in any region shall have the obligation to execute or cause to be executed such decisions or orders.

**63. የወንጀል ተጠያቂነት**

1. በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ የማይወጣ ማንኛውም ሰው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234 አንቀጽ 62 እና 64 ባለዉ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ፍርድ ቤት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ሰዉ አግባብ ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**64.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. ይህ አዋጅ ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት መንገድ ፍጻሜ የሚያገኙ ይሆናል፡፡
2. የክልሉ ምክር ቤት የፍርድ ቤት የአስተዳደር ሠራተኞች ደንብ እስኪያወጣ ድረስ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ያለ የአስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት፣ ዝውውር፣ ስልጠና፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሁም የዲሲፕሊንና ተዛማጅ ጉዳዮች የዚህን አዋጅ አጠቃላይ ዓላማ በማይቃረን ሁኔታ ቀድሞ ስሰራበት በነበረው ህግ

**63. Criminal liability**

1. Any person who does not fulfill the obligations imposed by this proclamation shall be held criminally liable according to the provisions of the Federal Courts Proclamation No. 1234, Articles 62 and 64.
2. According to sub-article 3 of this Article, a person who is dissatisfied with the decision given by the court may appeal to the appropriate court.

**64. Transitory Provisions**

1) All pending cases shall continue to be heard by the same court in accordance with the former law;

2) The recruitment, employment, placement, promotion, transfer, training, salary and benefits of administrative staff in courts at all levels until the Council of the Region issues regulations on court Non-Judiciary staff, as well as disciplinary and related matters, in accordance with the effective law that does not inconsistent to the general objective of this proclamation

መሰረት ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፡፡

65. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

66.ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1) የክልሉ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተለይተው በተሰጡ ጉዳዮች ላይ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2) የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤
3) ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ የሚወጣን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

67.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ታህሳስ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አርባ ምንጭ**

**ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

shall continue to apply.

**65. Unapplicable laws**

1) Any proclamation, regulation, directive, or practice inconsistent to this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

**66. Power to issue Regulations and Directives**

1) The state council may enact regulations on issues specified in this proclamation.
2) The Regional Judges Administration Plenum may issue a directive to enforce this Proclamation;
3) The Supreme Court may issue directives for the enforcement of this Proclamation or any regulations issued pursuant to the Proclamation.

**67. Effective Date**

This proclamation shall enter into force on the 25th of December, 2023 up on its ratification by the State Council.

**Done at Arba Minch**

**December 25, 2023**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive of South Ethiopia Regional State**